# 592

የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ኦፍ ፡ አሜሪካ ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ክቡር ፡ ሚስተር ፡ ሪቻርድ ፡ ኒክሰን ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ እንዲጐበኙ ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በተደረገላቸው ፡ ጥሪ ፡ መሠረት፡ መጋቢት ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ከክብርት ፡ ባለቤታቸው ፡ ጋር ፡ በአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ የጦር ፡ አይሮፕላን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገቡ ። የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ልዑል ፡ መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ከብዙ ፡ መሳፍንቶና ፡ መኳንንት ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ በአይሮፕላን ፡ ጣቢያ ፡ ሲቀበሏቸው ፡ በተደረገላቸው ፡ የወዳጅነትና ፡ የክብር ፡ አቀባበል ፡ የተሰማቸውን ፡ ልባዊ ፡ ደስታ ፡ በመግለጽ ፡ በአውሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ለተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

## ልዑል ፡ ሆይ ።

## ክቡራን ፡ ክቡራት ።

በዚሁ ፡ ቀን ፡ የክቡር ፡ ፕሬዚደንት ፡ አ'ዘን ፡ ሐወርን ፡ የሰላምታ ፡ ቃልና ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ለማምጣት ፡ በመታደሌ ፡ ትልቅ ፡ ክብር ፡ ይሰማኛል ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የአሜሪካንን ፡ አገር ፡ ከጐበኙበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ክብርት ፡ ባለቤቴና ፡ እኔ ፡ ይህን ፡ አገር ፡ ለመጐብኘት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምኞት ፡ ስለነበረን ፡ ዛሬ ፡ እዚህ ፡ በመገኘታችን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ ተሰምቶናል ።

የኢትዮጵያ ፡ ወታደሮች ፡ የአገራቸውን ፡ ነፃነት ፡ መጠበቅ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በኰሪያም ፡ ያደረጉት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተጋድሎ ፡ ጭምር ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አድናቆት ፡ አስገኝቷል ።

ዛሬም ፡ በጣም ፡ አስደናቂ ፡ የሆነውን ፡ የክብር ፡ ዘብ ፡ ስጐበኝ ፡ በ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ. ም ፡ እንደ ፡ ኤውሮጳ ፡ አቆጣጠር ፡ ኰሪያን ፡ በጐበኘሁ ፡ ጊዜ፡ የኢትዮጵያን ፡ አስደናቂ ፡ ጀግኖች ፡ እዚያ ፡ አይቼ ፡ የነበረውን ፡ አስታወሰኝ ። ምንም ፡ እንኳን ፡ እዚህ ፡ የምናደርገው ፡ ጉብኝት ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ ቢሆን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ከባለሥልጣኖች ፡ ጋር ፡ የኢትዮጵያንና ፡ የዩናይትድ ፡ ስቴትስን ፡ የጋራ ፡ ጉዳዮች ፡ ለመነጋገርና ፡ እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ካሉ ፡ ሰዎች ፡ ጋርም ፡ ግንኙነት ፡ ለማድረግ ፡ ተስፋችን ፡ ነው ።



ንግግሬንም ፡ በማቆም ፡ ወደ ፡ አእሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ እኛን ፡ ለመቀበል ፡ የመጣችሁትን ፡ ሁሉ ፡ አመሰግናችኋለሁ ፡ እንዲሁም ፡ በዚች ፡ በአበባይቱ ፡ ከተማ ፡ የምትገኙ ፡ ለሚስስ ፡ ኒክሰን ፡ አበባ ፡ ስለ ፡ አበረከታችኋት ፡ ያለን ፡ ስሜት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይህም ፡ የበልግ ፡ ዝናብ ፡ የኛንና ፡ የናንተን ፡ መንፈስ ፡ ሊያቀዘቅዘው ፡ እንደማይችል ፡ በእርግጥ ፡ አምናለሁ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ እኔ ፡ ከምመጣበት ፡ ካሊፎርኒያ ፡ ከሚባለው ፡ አገር ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ አየር ፡ ያልተለመደ ፡ አየር ፡ ብለን ፡ ብንጠራውም ፡ የአየሩ ፡ መለወጥ ፡ የኛን ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ስሜት ፡ አልለወጠውም ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የእናንተንም ፡ እንዳልለወጠው ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ።

---

# 593

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ክቡር ፡ ሚስተር ፡ ኒክሰንን ፡ ተከትለው ፡ የመጡትን ፡ የአሜሪካ ፡ ጋዜጠኞች ፡ መጋቢት ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተቀብለው ፡ ከአነጋገሩዋቸው ፡ በኋላ ፡ ለጋዜጠኞቹ ፡ የተናገሩት፡ ቃል ።

ዛሬ ፡ እዚህ ፡ መገኘታችሁ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ አሜሪካንን ፡ በጐበኘንበት ፡ ጊዜ ፡ የአሜሪካ ፡ ጋዜጠኞች ፡ በጋለ ፡ የወዳጅነት ፡ ስሜት ፡ እንደተቀበሉን ፡ ያስታውሰናል ። እዚህ ፡ የምትቆዩበት ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝና ፡ ጠቃሚም ፡ እንዲሆንላችሁ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

የምክትል ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ኒክሰንና ፡ የባለቤታቸው ፡ ጕብኝት ፡ እኛ ፡ አሜሪካንን ፡ በጐበኘንበት ፡ ጊዜ ፡ የተመሠረተውን ፡ ወዳጅነት ፡ ለማደስና ፡ እንደዚሁም ፡ ለሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ የጋራ ፡ ጉዳይ ፡ በሆኑት ፡ ነገሮች ፡ ለመመካከር ፡ ለጋራ ፡ ጥቅማችንም ፡ ግንኙነታችንን ፡ በበለጠ ፡ ለማጠንከር ፡ የሚያስችለን ፡ መልካም ፡ አጋጣሚ ፡ ነው ።

ምክትል ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ኒክሰን ፡ በዋና ፡ ከተማችን ፡ የሚቆዩበት ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ እጅግ ፡ አጭር ፡ ቢሆን ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ችግራችንና ፡ ጉዳያችንንም ፡ ይህንኑም ፡ ለመወጣት ፡ የምናደርገውን ፡ ጥረትና ፡ ያለንን ፡ ፕላን ፡ በቅርብ ፡ ለማወቅ ፡ ችለው ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ሲመለሱ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሚመጡት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ የሚገጥሙዋትን ፡ ጉዳ

ዮች ፡ በአሜሪካ ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ እንዲታወቁ ፡ ለማድረግ፡ ይረዳቸው ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

በውጭ ፡ አገር ፡ ግንኙነታችን ፡ ረገድ ፡ ዓላማችን ፡ ፖሊሲያችንና ፡ ሁልጊዜም ፡ በመንግሥታችን ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ክርክር ፡ ሁሉ ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ይገባል ፡ በማለት ፡ እምነት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ። በስዊስ ፡ ካናል ፡ ጉዳይም ፡ በተደረገው ፡ ጥረት ፡ ተገቢና ፡ ትክክለኛ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲገኝለት ፡ በበኩላችን ፡ የደከምንበት ፡ ይህንኑ ፡ ዓላማ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የሚያገባቸው ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ የግብፅም ፡ እንደዚሁ ፡ በካናሉ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆኑት ፡ አገሮች ፡ መብትና ፡ ጥቅም ፡ የሚጠበቅበትን ፡ ዘዴ ፡ ለመፍጠር ፡ ተባብረው ፡ እንዲሠሩ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

ስለሁንጋሪ ፡ ጉዳይም ፡ ባለፈው ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በዚሁ ፡ አገር ፡ የተደረገውን ፡ አሳዛኝ ፡ የሆነ ፡ ብጥብጥና ፡ የደም ፡ መፋሰስ ፡ በጣም ፡ አሳዝኖናል ። በሚቻለንም ፡ ረድተናል ።

በነዚህና ፡ እነዚህንም ፡ በመሳሰሉ ፡ ጉዳዮች ፡ ኢትዮጵያና ፡ አሜሪካ ፡ እየራሳቸው ፡ ያላቸው ፡ የኢንተርናሺናል ፡ ፖሊሲ ፡ የዓለም ፡ ሰላም ፡ እንዲጠበቅና ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የወደፊት ፡ እድገት ፡ እንዲሻሻል ፡ ባላቸው ፡ ጥልቅ ፡ ምኞት ፡ የተመራ ፡ ነው ። ፕሬዚዳንት ፡ አይዘንሐወር ፡ ስለ ፡ መካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ያቀዱት ፡ ፕላን ፡ በዚህ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ የሚገኙትን ፡ አገሮች ፡ እንዲደረጁና ፡ ነፃነታቸው ፡ ጠብቀው ፡ እንዲበለጽጉ ፡ የሚረዳቸው ፡ ይሆናል ፡ ብላ ፡ በማመን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ፕላኑን ፡ ከደገፉት ፡ የመጀመሪያ ፡ አገሮች ፡ አንደኛዋ ፡ ናት ።

በመናገሻ ፡ ከተማችን ፡ በቈያችሁበት ፡ አጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በአሜሪካ ፡ የጋራ ፡ መዋጮ ፡ የሚካሄዱትን ፡ ሥራዎች ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ አግኝታችሁ ፡ ሳትጐበኙ ፡ አልቀራችሁም ። ይህን ፡ እርዳታ ፡ በምስጋና ፡ የተቀበልነው ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ በዚህ ፡ እርዳታ ፡ እስካሁን ፡ የተሠራው ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ የሚቻለውን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞአል ። ለማለት ፡ በፍጹም ፡ አያስደፍርም ። ኢትዮጵያ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቷን ፡ አስፋፍታ ፡ የሕዝቧን ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ እንድትችል ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ፡



እርዳታ ፡ ያስፈልጋል ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ሁለቱም ፡ አገሮቻችን ፡ ከልብ ፡ ለሚጥሩበት ፡ ለዓለም ፡ ሰላም ፡ ጥበቃና ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የኑሮ ፡ እድገት ፡ መሻሻል ፡ ካሁኑ ፡ የበለጠ ፡ ለመርዳት ፡ የሚያስችላት ፡ የደረጀ ፡ ችሎታ ፡ እንዲኖራት ፡ ያስፈልጋል ።

የምክትል ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ኒክሰን ፡ ጉብኝት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ ጉብኝታቸው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ካስረዳነው ፡ ጉዳይ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ሲታይ ፡ ነው ።

---

# 594

የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ኦፍ ፡ አሜሪካ ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ክቡር ፡ ሚስተር ፡ ኒክሰን ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በተደረገላቸው ፡ ጥሪ ፡ መሠረት ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ ለሁለት ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ከጐበኙ ፡ በኋላ ፡ መጋቢት ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ ለመመለስ፡ በአእሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ተገኝተው ፡ ሳሉ ፡ ከመሳፈራቸው ፡ በፊት ፡ በአውሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ለተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ የገለጹት ፡ የደስታ ፡ መግለጫና ፡ የማሰናበቻ ፡ ንግግር ።

እኔና ፡ ባለቤቴ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ሳንቆይ ፡ መሄዳችንን ፡ አውቃለሁ ። እኛን ፡ ለመሸኘት ፡ ወደ ፡ አይሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ የመጣችሁትን ፡ ሁሉ ፡ እዚህ ፡ በመገኘታችሁ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ደስታ ፡ እንደተሰማን ፡ ለመግለጥ ፡ እያዳገተኝ ፡ ለአደረጋችሁልን ፡ አክብሮት ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ ምስጋናችንን ፡ እናቀርብላችኋለን ።

ባሌቤቴና ፡ እኔ ፡ ራሴም ፡ ጭምር ፡ እዚህ ፡ በተደረገልን ፡ አቀባበል ፡ ተደንቀናል ፡ በተለይ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተሰብ ፡ የመንግሥታችሁ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ያሜሪካ ፡ አምባሳደር ፡ ረዳቶቻቸውና ፡ የዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ ሠራተኞች ፡ ያደረጉልን ፡ አቀባበል ፡ የሚዘነጋ ፡ አይደለም ።

የአሜሪካና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የተሳሰረ ፡ አንድነት ፡ ያላቸው ፡ በመሆናቸው ፡ ወደፊትም ፡ አገሪቱንና ፡ ሕዝቦቿን ፡ ለማየት ፡ እንድንችል፡ ያለን ፡ ምኞት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ለሆነ ፡ ምኞት

በመተባበር ፡ አብረን ፡ እንደመሥራታችን ፡ መጠን ፡ ለወደፊቱም ፡ እንዲሁ በወዳጅነት ፡ እንደምንሠራ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ።

# 595

የ፲፬ቱ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ከጥር ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፡ ዓመታዊ ፡ ጉባኤ ፡ ሲያደርጉ ፡ ሰንብተው ፡ ጉባኤውን ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ መጋቢት ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፱ ፡ ዓ. ም. በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ተሩብ ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀርበው ፡ ሲሰናበቱ ፡ የሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሥራ ፡ አሥኪያጅ ፡ አቶ ፡ አበበ ፡ ጥላሁን ፡ በሥራ ፡ ጓደኞቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ የተናገረው ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ)የአቶ ፡ አበበ ፡ ጥላሁን ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የአንድ ፡ ሕዝብ ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ማሻሻያ ፡ የመብት ፡ መጠበቂያ ፡ የጥቅምና ፡ የጉዳት ፡ መለያ ፡ በጠቅላላው ፡ የአንድ ፡ አገር ፡ ትልቅነት ፡ የተረጋገጠ ፡ ዋስትና ፡ ማግኛ ፡ ትምህርት ፡ መሆኑን ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ተገንዝበው፡ ለኢትዮጵያ ፡ እድገት ፡ ከሚያክሙላት ፡ ብዙ ፡ ታላቅ ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ ትምህርት ፡ የመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ።

ዛሬ ፡ ከፍተኛውን ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ይዘው ፡ የሚገኙት ፡ አገሮች፡ አሁን ፡ አሉበት ፡ ሥልጣኔ ፡ ደረሱ ፡ በየጊዜው ፡ የገጠማቸውን ፡ ችግርና ፡ ችግሩንም ፡ በምን ፡ መልክ ፡ እንደተራመዱት ፡ ያለፈ ፡ ታሪካቸውን ፡ በመመልከት ፡ ለአገራችንና ፡ ለሥልጣኔያችን ፡ የሚጠቅመውን ፡ እየመረጥን ፡ በመሥራት ፡ በትምህርት ፡ በኩል ፡ እስከዛሬ ፡ የተፈጸመውን ፡ ሥራ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ጥልቅ ፡ አስተዋይነት ፡ ትምህርት ፡ በሰፊው ፡ መዘርጋት ፡ ከተጀመረበት ፡ ከዚህ ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ ጋር ፡ ስናወዳድረው ፡ በጠቅላላው ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ለኢትዮጵያና ፡ ለተወዳጅ ፡ ሕዝብዎ ፡ ያደረጉት ፡ ከፍተኛ፡ ድካምና ፡ ወደፊት ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ጥረት ፡ የምንጨብጠውን ፡ ከፍተኛ፡ ሥልጣኔ ፡ በጥልቅ ፡ እናስበዋለን ።



ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ተወዳጅ ፡ ሕዝብዎ ፡ የኑሮ ፡ ደረጃውን ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ እንዲችልና በትምህርትም ፡ ከፍ ፡ እንዲልና ፡ ትምህርት ፡ በሙሉ ፡ እንዲደርሰው ፡ ለማድረግ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ካሉት ፡ ብዙ ፡ ሐሳቦች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ የኮሚዩኒት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በየመንደሩ ፡ መቋቋም ፡ መሆኑን ፡ አርቆ ፡ በማሰብ ፡ ሥራውን ፡ የሚመሩ ፡ መምህራን ፡ የሚሠለጥኑበት ፡ ሁለት ፡ የመምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በአሁኑ ፡ ዓመት ፡ ተከፍተው ፡ ሥራውን ፡ እንዲጀምሩ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ስለፈቀደ ፡ የእነዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሥራ ፡ የተቃና ፡ እንዲሆን ፡ የትምህርትና ፡ የሥነ ጥበብ ሚኒስትር ፡ አስፈላጊውን ፡ ሁሉ ፡ በማከናወን ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

ከእነዚህም ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የሚወጡት ፡ መምህራን ፡ ግርማዊነትዎ ስለመሠረቱ ፡ ትምህርት ፡ የሰጠውን ፡ አዋጅ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውሉ ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡ በባላገር ፡ የሚኖረውን ፡ የለም ፡ መሬት ፡ ባለርስት ፡ የሆነውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ የእርሻ ፡ የቤት ፡ አሠራር ፡ የጤና ፡ አጠባበቅ ፡ የከብት ፡ እርቢና ፡ ሌላም ፡ ይህንና ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ የባላገር ፡ ሕዝብ ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ ለማድረጊያ ፡ ዘዴዎች ፡ የሚያስተምሩ ፡ ስለሆኑ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ለሥልጣኔውና ፡ ፡ ለኑሮው ፡ ምቾት ፡ ለጤናውና ፡ ለመልካም ፡ አስተዳደሩ ፡ በጥብቅ ፡ የሚያስቡለት ፡ ሕዝብዎ፡ መልካም ፡ አኗኗርና ፡ አጠባበቅ ፡ የመጀመሪያውን ፡ መቅድም ፡ ነጋሪዎች፡ ይሆናሉ ።

በ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በትምህርትና ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ በ፲፬ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ በአዲስ ፡ አበባና ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ቍጥር ፡ ፬፻፸፩ ፡ ሲሆኑ ፡

| | ወንድ ፡ | ሴት፡ | ድምር |
|---|---|---|---|
| (፩) በመንግሥት ፡ ፩ኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ | 83.409 | 17.567 | 100.976 |
| (፪) በመንግሥት ፡ ፪ኛ ፡ ደረጃ ፡ ት/ ቤቶች ፡ በመምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ በተግባረ ፡ እድ ፡ ት/ ቤቶች ፡ በንግድና ፡ በእርሻ ፡ ት/ ቤቶች ፡ | 2.941 | 291 | 3.232 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| (፫) በዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ በቴክኖሎጅና ፡ በሕንፃ ፡ ኮሌጆች ፡ | 246 | 10 | 256 |
| (፬) በቤተ ፡ ክህነት ፡ ት ቤቶች ፡ የታወቁት | 25.783 | 1.293 | 27.076 |
| (፭) በሚስዮንና ፡ በግል ፡ ት ቤቶች | 36.488 | 5.286 | 41.777 |
| (፮) የማታ ፡ ትምህርት ፡ የሚቀጥሉ ፡ | 4.394 | 133 | 4.527 |
| (፯) የሠመረተ ፡ ትምህርት ፡ ተማሪዎች ፡ | 13.110 | 237 | 13.347 |
| በጠቅላላው ፡ | 166.371 | 24.820 | 191.191 |

ተማሪዎች ፡ በትምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ።

በአገራችን ፡ ትምህርት ፡ ከፍተኛውን ፡ ደረጃ ፡ ያገኙት ፡ መንፈሳዊ
ነት ፡ የሚሰማቸው ፡ መነኮሳት ፡ ወይም ዓለማዊ፡ ሰዎች ፡ በአንዳንድ ፡
አድባራት ፡ ከፍተኛ ፡ መንደሮችና ፡ ከተሞች ፡ እየተጠጉ ፡ ያለገንዘብ ፡
ወዮንም ፡ በመጠነኛ ፡ ደመወዝ ፡ በሚያስተምሩ ፡ መምህራን ፡ የአገራችንን
ትምህርት ፡ የሚማሩ ፡ ተማሪዎች ፡ ቊጥር ፡ የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ በባ
ጀት ፡ ከሚያስተዳድራቸው ፡ ይልቅ ፡ የበለጡ ፡ መሆናቸው ፡ ተገምቷል ።

በተለይም ፡ ይህ ፡ ትምህርት ፡ ተስፋፍቶ ፡ በሚሰጥባቸው ፡ በጐንደር፡
በጐጃም ፡ በትግሬ ፡ በሸዋ ፡ በሚገኙት ፡ አድባራት ፡ የሚማሩት ፡ ተማሪ
ዎች ፡ ቊጥር ፡ አይደለም ። ወደፊት ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ተከፋፍለው ፡ የሚ
ገኙት ፡ በጠቅላላው ፡ በየአድባራቱና ፡ በቤተክህነት ፡ በመንደር ፡ የሚገ
ኙትንም ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ተማሪዎች ፡ ቊጥር ፡ ጠንቅቆ ፡ ማወቅና ፡
የተጣራ ፡ እስታስቲክ ፡ መያዝ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ በመረዳት ፡ ሥራ
ውን ፡ በጥንቃቄ ፡ ለማካሄድ ፡ ስለሚቻልበት ፡ ዘዴ ፡ ከአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒ
ስቴር ፡ ከቤተክህነት ፡ ወኪሎች ፡ ጋር ፡ በአሁኑ ፡ ስብሰባችን ፡ ተነጋግረን
በት ፡ በሐሳቡ ፡ ስለተግባባን ፡ ትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ከእነዚህ ፡ መሥሪያ፡
ቤቶች ፡ ጋር ፡ ተስማምቶ ፡ በሚሰጠን ፡ ቋሚ ፡ መምሪያ ፡ መሠረት ፡ በመ
ጭው ፡ ዓመት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ በትም
ህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ወጣቶች ፡ ትክክለኛ ፡ ቊጥር ፡ እንደምናቀ
ርብ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

እስካሁን ፡ በተደረገው ፡ ጥናት ፡ መሠረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡



የሴቶች ፡ ተማሪዎች ፡ ቊጥር ፡ ከሚያንስበት ፡ ምክንያት ፡ አንዱ ፡ በተለይ፡
ለሴቶች ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ማሻሻያ ፡ አስፈላጊና ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ከ
ዚህ ፡ ቀደም ፡ የተዘጋጅ ፡ ፕሮግራምና ፡ በተለይም ፡ የተቋቋሙት ፡ ት/ቤቶ
ች ፡ በቂ ፡ ባለመሆናቸው ፡ ምክኒያት ፡ እንደሆነ ፡ ተረጋግጧል ።

ስለዚህ ፡ በ፲፱፻፸፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ የተሰጠውን ፡ መሪ ፡
ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ልዩ ፡ ፕሮግራም ፡ በአሁኑ ፡ ዓመት ፡ ስለተ
ዘጋጀና ፡ ይህም ፡ ፕሮግራሙ ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሴቶችን ፡ ልጆች ፡
ወደ ፡ ሁለተኛ ፡ ት/ ቤት ፡ ለማድረስ ፡ የሚረዳ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የወደ
ፊት ፡ የኑሯቸውን ፡ ዕድል ፡ የሚያቃና ፡ መሆኑ ፡ በትምህርትና ፡ ሥነ ፡
ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ በኩል ፡ ተጠንቶ ፡ በአሁኑ ፡ ዓመት ፡ ስብሰባችን ፡ ስለ
ቀረበልን ፡ ጠቃሚነቱን ፡ ተረድተን ፡ እንዲሠራበት ፡ ተስማምተናል ።

ይህንን ፡ ፕሮግራም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚቻለው ፡ ከዚህ ፡
ቀደም ፡ በ፲፱፻፸፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአደረግነው ፡ ጉባኤ ፡ ተነጋግረን ፡ በተስማማ
ንበት ፡ መሠረት ፡ የተለየ ፡ የሴቶች ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ት ቤት ፡
ሲቋቋም ፡ መሆኑ ፡ ስለተረጋገጠ ፡ የዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መቋቋም ፡
ሥራ ፡ በቶሎ ፡ እንዲጀምር ፡ አስፈላጊ መሆኑን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ እናስታ
ውሳለን ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የሴቶች ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡
በተለይ ፡ ባልተቋቋሙባቸው ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ አንዳንድ ፡ የተለየ ፡
የሴቶች ፡ ት/ቤት ፡ እንዲቋቋምላቸውና ፡ በአዲስ ፡ አበባም ፡ ብዙ ፡ ልጅ ፡
አገረዶች ት/ቤት ፡ ለመግባት ፡ ጠይቀው ፡ ቦታ ፡ ሳያገኙ ፡ ቀርተው ፡ የተ
መለሱ ፡ ስላሉ ፡ ተጨማሪ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በተጨማሪ ፡ እንዲቋቋሙ
ማስፈለጉን ፡ አጥንተናል ።

ግርማዊነትዎ ፡ ትምህርት ፡ የነፃነት ፡ ዋስ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን
መሪ ፡ ቃል ፡ ተወዳጁ ፡ ሕዝብዎ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በየዘመኑ ፡ የትም
ህርት ፡ ቤቶች ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ በትምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ የሚገኙት፡
ወጣቶች ፡ እየበረከቱ ፡ በመሄዳቸው ፡ ከዛሬ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ በት
ምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ከነበሩት ፡ ወጣቶች ፡ ይልቅ ፡ ዛሬ ፡ በትምህርት ፡
ገበታ ፡ ላይ ፡ የሚገኙት ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ ያህል ፡ ሆነዋል ።

የወጣቶች ፡ ቊጥር ፡ መጨመር ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡
ማለት ፡ ወጭውን ፡ እያበረከተውና ፡ እያሳደገው ፡ በመሄዱ ፡ ከመሬት ፡

ላይ ፡ እንድናገኝ ፡ የተፈቀደልን ፡ ገቢ ፡ በየዘመኑ ፡ እያደገ ፡ የማይሄድ ፡ የተቆረጠ ፡ ገቢ ፡ በመሆኑ ፡ በተለይ ፡ በአሁኑ ፡ ዓመት ፡ በገንዘብ ፡ በኩል፡ የደረሰብን ፡ ችግር ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ያቀረበውን ፡ የገቢ ፡ ምንጭ ፡ ከ፲፱፻፷፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መጀመሪያ ፡ አንስቶ ፡ እንድንሠራበት ፡ ግር ማዊነትዎ ፡ እንዲፈቅድልን ፡ በፍርሃት ፡ እየለመንን ፡ ትግሬ ፡ ወሎ ፡ ጎ ጃምና ፡ ኢሉባቦር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ በተለይ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ያቀረ ቡት ፡ ማስታወሻ ፡ አስቸኳይ ፡ ውሳኔ ፡ መጠየቁን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ በታ ላቅ ፡ ትሕትና ፡ እናስታውሳለን ።

የሰውም ፡ ዕድል ፡ በዛሬው ፡ ዘመን ፡ ከአስተዳደጉና ፡ ከትምህርት ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የሰጠውን ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ በማሰብ ፡ ዛሬ ፡ ማንኛውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ለመማር ፡ የማይፈቅድ ፡ ፈጽሞ ፡ አይገኝም ።

ይህንንም ፡ የጋለ ፡ ፍላጎቱን ፡ ያበረታታው ፡ የመሠረተ ፡ ትምህርት ፡ አዋጅ ፡ መታወጅ ፡ ነው ፡ ይህንንም ፡ ልግስና ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ የተገነዘ በው ፡ ሕዝብዎ ፡ መሠረተ ፡ ትምህርት ፡ በየቦታው ፡ እንዲከፈትለት ፡ የሚ ያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ እየበረከተ ፡ እንደሄደ ፡ ነው ፡ ይህን ንም ፡ የሕዝቡን ፡ ፍላጎት ፡ በተቻለ ፡ ለማርካት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ባሉን ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ያሉንን ፡ መምህራንና ፡ የከፍተኛ ፡ ክፍል ፡ ተ ማሪዎች ፡ ከተወሰነላቸው ፡ ሥራና ፡ ትምህርት ፡ በላይ ፡ በማሠራት ፡ ትም ህርትን ፡ እንዲያስተምሩ ፡ በማበረታታት ፡ ላይ ፡ እንገኛለን ።

እስካሁን ፡ የሐሳባችን ፡ ደጋፊ ፡ በሆኑ ፡ መምህራንና ፡ ተማሪዎች ፡ እየተረዳን ፡ ዕድሜያቸው ፡ ከአሥራ ፡ ስድስት ፡ እስከ ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡ የሆናቸው ፡ ሰዎች ፡ ቍጥር ፡ አሥራ ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሰባት ፡ ደርሷል ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ መሠረተ ፡ ትምህርት ፡ ለመማር፡ በጣም ፡ ሲጓጓ ፡ ሐሳቡን ፡ በሚቻል ፡ መጠን ፡ ለመፈጸም ፡ ለትምህርት ፡ መማሪያ ፡ ለመምህራን ፡ ጉርሻ ፡ ወጭ ፡ ስለሚያስፈልገው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ እንዲውል ፡ በትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ በኩል ፡ ተጠንቶ ፡ የቀረበውን ፡ ባጀት ፡ እንዲፈቀድልን ፡ ግርማዊነትዎን ፡ እንለምናለን ።

ባንድ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ሕዝቦች ፡ ተረዳድተው ፡ ተግ



ባብተውና ፡ ተስማምተው ፡ ሲሠሩ ፡ የመሪውን ፡ የሥራ ፡ ሸክም ፡ የሚያቃ ልሉ ፡ መሆናቸውን ፡ በመገመት ፡ በአሁኑ ፡ ዓመት ፡ ስብሰባችን ፡ ከሌሎቹ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ጋር ፡ የሚያገናኙንን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ አጥንተን ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከታቸው ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ወኪሎች ፡ ባሉበት ፡

(፩ኛ) በጠረፍ ፡ አገሮች ፡ ስለሚቋቋሙት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችና ፡ የሚቋቋሙበትን ፡ ሁኔታ ፡

(፪ኛ) በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ በትምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ የሚገኙትን ፡ ወጣቶች ፡ ቍጥር ፡ በትክክል ፡ ለማወቅ ፡ የሚ ቻልበት ፡ ዘዴ ፡

(፫ኛ) በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ መሬቶች ፡ በትክክል ፡ ቀላድ ፡ ቢጣልባቸው ፡ ለትምህርት ፡ ሚኒስቴርም ፡ ሆነ ፡ ለገን ዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስለሚሰጡት ፡ ተጨማሪ ፡ ገቢ ፡

(፬ኛ) ስለተማሪዎች ፡ ጤና ፡ አጠባበቅ ፡ ሌላ ፡ ይህንንና ፡ ይህን ፡ ስለ መሳሰሉት ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ ሰፊ ፡ ንግግር ፡ ተደርጎ ፡ ማስታወሻው ፡ በትም ህርትና ፡ በሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ በኩል ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ የሚቀርብ ፡ ስለሆነ ፡ ይኸው ፡ በቶሎ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲያገኝልን ፡ ግርማዊነትዎን ፡ በፍር ሃት ፡ እንለምናለን ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ዕድሜያችን ፡ ቆይቶ ፡ ግዛታችን ፡ ከጠ ላት ፡ ቀንበር ፡ ሥር ፡ ነፃ ፡ ወጥቶ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕፃናት ፡ ለማስተማርና ፡ ወጣቶችን ፡ በዕውቀት ፡ ለማጐልመስ ፡ የትምህርት ፡ ቤቶችንም ፡ ለማስፋ ፋት ፡ በመቻላችን ፡ ፈጣሪያችንን ፡ እየመላለስን ፡ የምናመሰግነው ፡ ስለዚ ህ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በከፈትን ፡ ጊዜ ፡ የነበሩትን ፡ ተማሪዎች ፡ ቍጥር ፡ ማነስ ፡ ዓይተን ፡ ወደፊት ፡ የሚሆን

ውን ፡ በማሰብ ፡ ቍጥራችሁ ፡ አሁን ፡ ባየነው ፡ ተወስኖ ፡ የሚቀር ፡ አይደለም ፡ ወደፊት ፡ የሚነሱትም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተማሪዎች ፡ በብዙ ፡ ሺህ ፡ የሚቆጠሩ ፡ ይሆናሉ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱም ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ አይቀርም ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ የሆኑ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ይሠራሉ ። ብለን ፡ ተናግረን ፡ ነበር ። አሁንም ፡ የሰው ፡ ምኞት ፡ የሚፈጽም ፡ እግዚአብሔር ፡ በዕድሜ ፡ አቆይቶን ፡ አሁን ፡ እንደተናገራችሁት ፡ የተማሪዎቹ ፡ ብዛት ፡ የትምህርት ፡ ቤቶቹም ፡ ቍጥር ፡ እየጨመረ ፡ በመሄዱና ፡ ምኞታችንም ፡ ከፍ፡ ካለ ፡ ደረጃ ፡ በመድረሱ ፡ እጅግ ፡ አስደስቶናል ።

ይህም ፡ ምኞታችን ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ ላይ ፤ ሊደርስ ፡ የቻለው ፡ ረዳት ፡ በማግኘታችን ፡ ነው ። በዚህም ፡ ጉዳይ ፡ ዋኖቹ ፡ ረዳቶች ፡ እናንተ ፡ ናችሁ ፡ እረዳትም ፡ ቢገኝ ፡ ተቀባይ ፡ ካልተገኘ ፡ ረዳት ፡ ብቻውን ፡ ማንን፡ ይረዳ ፡ ነበር ። ሕዝባችን ፡ የትምህርት ፡ ጥቅም ፡ በማወቁና ፡ ይልቁንም ፡ በጠላት ፡ ጊዜ ፡ **አለመማር ፡ ታላቅ** ፡ ውርደት ፡ የሚያስከትል ፡ መሆኑን ፡ ተገንዝቦ ፡ ጠላት ፡ ከወጣና ፡ እኛም ፡ ከተመለስን ፡ በኋላ ፡ ከመቼውም ፡ ይልቅ ፡ በሚያስደንቅ ፡ ትጋት ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በመሯሯጡ ፡ ለትምህርት ፡ መስፋፋት ፡ ያቀድነው ፡ ፕሮግራም ፡ ከፍ ፡ ወዳለው ፡ ደረጃ ፡ ደርሶ ፡ እናየዋለን ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ በደንብ ፡ የተቋቋሙት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ለመላው ፡ ሕዝባችን ፡ በቂ ፡ አለመሆናቸውን ፡ ገምተን ፡ ሰው ፡ ዕድሜዩ ፡ በዛ ፡ ብሎ ፡ በስንፍናው ፡ ባለመማር ፡ ጉዳት ፡ እንደሚያገኘው ፡ አውቀን ፡ ከዚህ የምንድንበትን ፡ መሠረት ፡ ትምህርት ፡ አቋቋምን ።

አሁን ፡ በተናገራችሁት ፡ በተማሪዎቹ ፡ ዝርዝርና ፡ ድምር ፡ በትምህርት ፡ ቤቱም ፡ ብዛት ፡ በሕዝባችንም ፡ የትምህርት ፡ ፍላጎት ፡ ደስ ፡ ብሎናል ፡ ወደፊት ፡ ከዚህ ፡ እየበለጠ ፡ እንዲሄድ ፡ የምንመኘው ፡ ነው ።

ለሰው ፡ ልጅ ፡ ትምህርት ፡ አስፈላጊው ፡ ሲሆን ፡ ከትምህርት ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ መልካም ፡ ባሕርይ ፡ ማግኘት ፡ ያስፈልገዋል ። እንዲሁም ፡ የጥንት ፡ አባቶቻችን ፡ ልማድና ፡ ባህል ፡ እንዳይጠፋ ፡ አገር ፡ አለኝ ፡ ያባቶቼ ፡ ልማድ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ እንዲችል ፡ ማስጠናት ፡ ያስፈልጋል።

ስለዚህ ፡ ትምህርት ፡ የአባቶችን ፡ ልማድ ፡ አለመተውና ፡ በጠቅላላው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደተናገርነው ፡ የሁሉ ፡ ነገር ፡ መሣሪያ ፡ የሆነውን ፡



እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ማናቸውንም ፡ የታሰበውን ፡ ነገር ፡ ከፍጻሜ ፡ ያደርሰዋል ።

ያባቶችን ፡ ሃይማኖት ፡ ማክበር ፡ ለአንድ ፡ ሕዝብ ፡ ኵራቱ ፡ ነው ፡ ይህንንም ፡ ለማረጋገጥ ፡ የሌላው ፡ ዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ በሃይማኖታቸው ፡ እንደምን ፡ እንደሚኮሩበትና ፡ እንደምን ፡ አድርገው ፡ መሥዋዕት ፡ እንደሚሆኑለት ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ሳትመለከቱትና ፡ ሳታውቁት ፡ አልቀራችሁም ።

ታሪክም ፡ ሃይማኖትም ፡ የአባት ፡ ልማድም ፡ ሦስቱም ፡ የሌለው ፡ ነፃነትም ፡ አገርም ፡ እናት ፡ አባትም ፡ እንደሌለው ፡ የሚቆጠር ፡ ነውና ፡ እነዚህን ፡ ሦስቱን ፡ መሠረታዊያን ፡ ነገሮች ፡ ሕዝቡም ፡ ተማሪዎቹም ፡ በአእምሮአቸው ፡ ቀርፀው ፡ እንዲያኖራቸው ፡ ማድረግ ፡ አለባቸው ።

ስለተማሪዎቹ ፡ ኑሮ ፡ የገለጣችሁትን ፡ ሰምተናል ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ለተማሪም ፡ ጥቅሙ ፡ በደህና ፡ ቦታ ፡ ተቀምጦና ፡ ደህና ፡ ለብሶ ፡ ደህና ፡ በልቶ ፡ መማር ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

ለዚህም ፡ የቀድሞ ፡ አባቶቻችን ፡ ትምህርትን ፡ ለማግኘት ፡ የነበረባቸውን ፡ ችግርና ፡ ብርቱ ፡ ድካም ፡ ማስታወስ ፡ ይጠቅማል ፡ ይህም ፡ ከአንዱ ፡ አገር ፡ ወደሌላው ፡ አገር ፡ እየተሰደዱ ፡ በአኩፋዳ ፡ ሽምብራ ፡ እየለመኑ ፡ በልብስም ፡ ረገድ ፡ ታርዘው ፡ ይኸንን ፡ ሁሉ ፡ ችግር ፡ ከምንም ፡ ሳይቆጥሩት ፡ ትምህርታቸውን ፡ እየጠኑ ፡ ያገኙትን ፡ እውቀት ፡ ወደኛ ፡ ዘመን ፡ ማስተላለፋቸው ፡ ነው ። ከነርሱም ፡ ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ የመንፈስ ፡ ብርታት ፡ መውሰድ ፡ ይገባናል ።

በኛ ፡ ዘመን ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረድቶን ፡ ዘመናዊውን ፡ ትምህርት ፡ ለማስፋፋት ፡ ተችሏል ፡ ይህም ፡ ዘመናዊ ፡ ትምህርት ፡ ምቾት ፡ ካልተገኘለት ፡ ተማሪ ፡ ትምህርት ፡ አይገባውም ፡ ለማለት ፡ አይቻልምና ፡ በምቾትም ፡ ያለምቾትም ፡ ሕዝቡ ፡ ትምህርቱን ፡ እንዲገፋ ፡ እንድታበረታቱት ፡ ያስፈልጋል ።

እንደእውነቱ ፡ ሲመለከቱት ፡ ሰው ፡ ደልቶት ፡ ከሚማር ፡ ይልቅ ፡ ለሕይወቱ ፡ መደገፊያ ፡ የሚበቃውን ፡ ልብስና ፡ ምግብ ፡ ካገኘ ፡ አእምሮውን ፡ ለማብሰልና ፡ መንፈሱን ፡ ለማበረታታት ፡ መቻሉ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ።

በድሎት ፡ እማራለሁ ፡ የሚል ፡ ግን ፡ ለድሎቱ ፡ አገልጋይ ፡ ስ ሚሆን ፡ ከአእምሮው ፡ ላይ ፡ እሩቡን ፡ መክፈሉ ፡ አይቀርም ፡ ለሕይወቱ ፡ የሚበቃውን ፡ ያህል ፡ አግኝቶ ፡ የሚማር ፡ ግን ፡ ሙሉ ፡ አእምሮውንና ፡ መንፈሱን ፡ በትምህርት ፡ ላይ ፡ ሊያውለው ፡ ይችላል ።

ስለዚህ ፡ በችግር ፡ የሚያመካኙ ፡ ሰዎች ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች፡ ይህንኑ ፡ ሊታስረዷቸው ፡ ትችላላችሁ ። የሴቶችን ፡ ልጆች ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በየጊዜው ፡ በጐበኘን ፡ ጊዜ ፡ እንደተናገርነው ፡ ሴቶች ፡ ከወንዶች ፡ የሚበልጡበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። እንደዚሁም ፡ ሴቶች ፡ እንደደነባቸው ፡ ሴቶች፡ የሚሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ ስለዚህ ፡ ጥረታችን ፡ ሁሉ ፡ በትምህርት ፡ ተስተካክለው ፡ ወንዶችን ፡ እንዲረዱ ፡ ነው ።

አሁንም ፡ በትምህርት ፡ ቍጥራቸው ፡ አንሶ ፡ የሚታየው ፡ ሴቶች ፡ ተማሪዎች ፡ ብዛታቸው ፡ ከወንዶች ፡ ተማሪዎች ፡ እንዲስተካከል ፡ የበለጠ ፡ መድከም ፡ አለባችሁ ።

ለማናቸውም ፡ ነገር ፡ ገንዘብ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ተረድተነዋል ፡ ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ሊደረግ ፡ የሚገባውን ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ በሚገኘው ገቢ ፡ ብቻ ፡ ስንወስን ፡ ከውጪ ፡ አገርም ፡ በእርዳታ ፡ ከምናገኘው ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ፡ አብዛኛው ፡ ለትምህርት ፡ ክፍል ፡ እንዲውል ፡ እናደርጋለን ።

የትምህርትና ፡ የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴርነቱ ፡ ሥራ ፡ በቀጥታ ፡ እንዲመራ ፡ ያደረግነው ፡ የትምህርት ፡ ሥራ ፡ በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲስፋፋና ፡ ካሰብነው ፡ ግብ ፡ እንዲደርስ ፡ በማሰብ ፡ ነው ።

የትምህርት ፡ ሚኒስቴሩን ፡ ሥራ ፡ በቀጥታ ፡ የምንመራው ፡ እኛ ፡ ስለሆን ፡ እናንተም ፡ ከኛ ፡ በታች ፡ ሁናችሁ ፡ በየተሰጣችሁ ፡ ሥራ ፡ ኃላፊዎች ፡ በመሆናችሁ ፡ የተቀበላችሁትን ፡ አደራ ፡ በትጋት ፡ እንደ ትጠብቁት ፡ ይሁን ።

# 596

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መጋቢት ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በ፫ ፡ ሰዓት ፡ አባዲና ፡ የፖሊስ ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተገኝተው ፡ የፖሊስን ፡ ተግባር ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ታክቲክ ፡ ለተማሩትና ፡ ትምህርታቸውን ፡ ለፈጸሙት ፡ ለአምሳ ፡ ዘጠኝ ፡ እጩ ፡ መኰንኖች ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ሲሰጡ ፡ የተናገሩት ፡ መሪ ፡ ቃል ።



በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ያለበት ፡ ታላቅ ፡ ዕዳ ፡ ታማኝነት ፡ መሆኑን ፡ አትዘንጉ ።

ታማኝ ፡ መሆን ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ሀብትና ፡ ቅርስ ፡ ነው ። ታማኝነት ፡ ሃይማኖት ፡ ከከፍተኛ ፡ ቦታ ሚያደርስ ፡ የማይጠፋውንም ፡ ስም ፡ የሚያወርስ ፡ ነው ።

ታማኝነት ፡ ለፖሊስ ፡ መኰንኖች ፡ በጠቅላላው ፡ ለሕዝብ ፡ ፀጥታ ፡ ጥበቃ ፡ አላፊ ፡ ለሆኑት ፡ ፓሊሶች ፡ መጀመሪያ ፡ ተግባር ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ የፖሊስ ፡ መኰንኖች ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ትምህርታቸውን ፡ እየጨረሱ ፡ የሚወጡት ፡ ልጆች ፡ ቍጥር ፡ ከዓመት ፡ ወደ ፡ ዓመት ፡ እያደገ ፡ መሄዱን ፡ ስንመለከት ፡ እንኳ ፡ ከአገሩ ፡ ፍላጐት ፡ ጋራ ፡ ሲመዛዘን ፡ ያነሰ ፡ ሆኖ ፡ ብናገኘውም ፡ ወደፊት ፡ ያቀድነው ፡ ታላቅ ፡ ሥራውና ፡ ሠራዊቱ ፡ የሚስፋፋበት ፡ ፕላን ፡ ስለአለን ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

ባገኛችሁት ፡ የቴዎሪ ፡ ትምህርት ፡ መሠረት ፡ ያሳያችሁት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴ ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ እንዲገኝ ፡ አስቡ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ እናንተም፡ የሚያስመሰግነው ፡ ለሥራችሁም ፡ ጠንካራ ፡ ምርኩዝ ፡ የሚሆነው ፡ በገቢር ፡ አውላችሁት ፡ ሲታይ ፡ ነው ።

እናንተ ፡ ዛሬ ፡ በዕድሚያችሁም ፡ በትምህርታችሁም ፡ ወጣቶች ፡ ናችሁ ፡ ወደፊት ፡ በምትሰማሩበት ፡ ተግባር ፡ ብዙ ፡ ችግርና ፡ ተንኮል ፡ እንደሚገጥማችሁ ፡ ዕወቁ ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ ብልህ ፡ እንደ ፡ እርግብ ፡ የዋህ ፡ ሁኑ ፡ የተባለው ፡ ለዚህ ፡ ያገለግላል ፡ ከላይ ፡ የጠቀስንላችሁ ፡ ታማኝነት ፡ በውስጣችሁ ፡ ካለ ፡ ግን ፡ ክፉውን ፡ በበጎ ፡ ለማሸነፍ ፡ ትችላላችሁ ።

ከናንተ ፡ የሚጠበቀው ፡ ዓይነተኛ ፡ ተግባር ፡ ታማኝነትና ፡ ተግቶ ፡ መሥራት ፡ ለሕዝብ ፡ ትሁት ፡ አገልጋይ ፡ ለክፉ ፡ አድራጊም ፡ ተቀባይ ፡ መሆን ፡ ሕግን ፡ መጠበቅና ፡ ማስከበር ፡ የሕዝብ ፡ ፀጥታ ፡ በሚታወክበት ፡ ጊዜ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ሕይወትን ፡ መሥዋዕት ፡ ማድረግ ፡ እስከ ፡ መቁረጥ ፡ ድረስ ፡ መዘጋጀት ፡ ነው ።

ወደፊት፡ በሥራችሁ ፡ የሚገጥማችሁ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ችግር ፡ ታማኝነታችሁን ፡ ፍቱን ፡ የሚያደርግ ፡ አእምሮአችሁን ፡ የሚያስፋፋ ፡ ስለሆነ ፡ በ

ዚህ ፡ መንፈስ ፡ በመቀበል ፡ ተጠቀሙበት ፡ እንጂ ፡ የመመረርና ፡ የብስጭት ፡ መሣሪያ ፡ አታድርጉት ።

ለእናንተና ፡ ከናንተ ፡ በፊት ፡ ለነበሩት ፡ ወደፊትም ፡ በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለሚገኙት ፡ ወጣቶች ፡ ልናስገነዝባቸውና ፡ በአእምሮአችሁ ፡ ተቀርጾ ፡ እንዲኖር ፡ የምንመኘው ፡ ሕዝብ ፡ እምነቱንና ፡ ፍቅሩን ፡ በመንግሥቱና ፡ በፖሊስ ፡ ላይ ፡ ጥሎ ፡ እንዲኖር ፡ ፖሊስም ፡ በተግባሩ ፡ የሕዝብን፡ እምነትና ፡ ፍቅር ፡ የማረከ ፡ እንዲሆን ፡ ነው ።

እስካሁን ፡ ፖሊሶች ፡ በሥራቸው ፡ ያሥራቸውን ፡ የክብር ፡ ደረጃ ፡ መያዝ ፡ ጀምረዋልና ፡እናመሰግናቸዋለን ፡ ለተደከመላችሁ ፡ ድካምና ፡ ለተማራችሁት ፡ ትምህርት ፡ የሥራችሁን ፡ ፍሬ ፡ በማሳየት ፡ የተገባችሁ ፡ ሁናችሁ ፡ እንድትገኙ ፡ እንመኝላችኋለን ።

በትምህርታችሁ ፡ ላይ ፡ ከሕዝብ ፡ የተለየ ፡ ሰውነትን ፡ የመግዛት ፡ የመቅጣት ፡ ከተራ ፡ ቦታ ፡ ባለው ፡ ባሕርይ ፡ካላያችሁ ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ ልቡና ፡ ታዛቢ ፡ ነውና ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የሰጠናችሁ ፡ ምክርና ፡ ትእዛዝ ፡ ሁሉ ፡ መና ፡ ይሆናል ።

እውቀታቸውን ፡ ለናንተ ፡ በቅንነት ፡ ለማካፈል ፡ ያገለገሉንን ፡ የስዊድን ፡ መኰንኖች ፡ ከልብ ፡ እናመሰግናቸዋለን ።

---

# 597

የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በደብረ፡ ዘይት ፡ ከተማ ፡ የተሠራውን ፡ የወንጌላዊት ፡ ሚስዮን ፡ ኰሌጅ  መጋቢት ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ከእኩል ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ መርቀው ፡ ሲከፍቱ ፡ የኰሌጁ ፡ ዲሬክተር ፡ ምስተር ፡ ስቬን ፡ ሩቢንሰን ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የኰሌጁ ፡ ዲሬክተር ፡ ንግግር ።

## ልዑላን ፡ ክቡራንና ፡ ክቡራት ።

በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አስተማሪዎችና ፡ ተማሪዎች ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ይህን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለመጐብኘት ፡ ስለመጣችሁልን ፡ ምስጋናዬን ፡ አቀርባለሁ ።

የግርማዊነትዎ ፡ እዚህ ፡ መገኘት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ትምህርት ፡ እንዲ



ስፋፋ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ድካም ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ለኛ ፡ ለአስተማሪዎቹና ፡ ለተማሪዎቹ ፡ የማይረሳ ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚታወስ ፡ ተግባር ፡ መሆኑ ፡ በየበኩላችን ፡ ይሰማናል ።

የኢትዮጵያ ፡ ወንጌላዊት ፡ ኰሌጅ ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በጀርመን ፡ ሂርማንስበርግ ፡ ሚስዮን ፡ በኖርቤጅያን ፡ ሉተራን ፡ ሚስዮንና ፡ በስዊድን ፡ ወንጌላዊት ፡ ሚስዮን ፡ ኅብረት ፡ የቆመ ፡ ሲሆን ፡ ዋናው ፡ ዓላማው ፡ የሁለተኛን ፡ ደረጃ ፡ የመምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ለማስፋፋት ፡ ነው ።

ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እነዚህ ፡ የተባበሩት ፡ ሚስዮኖች ፡ አንድ ዓይነት ፡ የከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለማቋቋም ፡ ሐሳብ ፡ ነበራቸው ።

የዛሬ ፡ ሃምሳ ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የመጡት ፡ የወንጌል ፡ ሚሲዮናዊ ፡ ካርል ፡ ኬጀርክቢስት ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ የተለየ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በአዲስ አበባ ፡ እንዲያስፈልግ ፡ ጽፈው ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ሚስዮኖች ፡ ይህን ፡ ኰሌጅ ፡ ለማቋቋም ፡ እንዲችሉ ፡ ላበቃን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ እናቀርባለን ።

* * *

ለ)የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

አዲስ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በተከፈተ ፡ ቍጥር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ የእድገት ፡ ደረጃ ፡ አድርገን ፡ ስለ ፡ ምንቆጥረው ፡ ከታወቁት ፡ የክርስቲያን ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ፈቃደኛነት ፡ በመነጨው ፡ በጎ ፡ አድራጎትና ፡ እርዳታ ፡ የሠራውን ፡ ይህን ፡ ኮሌጅ ፡ ስንከፍት ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

ባለንጀራህን ፡ እንደራስህ ፡ አድርገህ ፡ ውደድ ፡ የተባለውን ፡ በመከተል ፡ የሦስቱ ፡ ሚስዮኖች ፡ ኅብረታዊ ፡ ድካምና ፡ ጥረት ፡ በሰጠው ፡ ፍሬ ፡ ይህን ፡ የተዋበ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለመሥራት ፡ በመቻላቸው ፡ ልናመሰግናቸው ፡ እንወዳለን ።

የሉተራን ፡ የዓለም ፡ ማኅበር ፡ መልእክተኛ ፡ የሆኑት ፡ ዶክተር ፡ ሶቪክ ፡ የዚህን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መከፈት ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ እዚህ ፡ በመገኘታቸው ፡ የወዳጅነት ፡ መልካም ፡ ስሜታችንን ፡ እየገለ

ጾን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ መርጃ ፡ እንዲሆን ፡ ይህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ስለመከፈቱ ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ለመልእክተኛነታቸው ፡ ለመጡበት ፡ ማኅበር ፡ ምስጋናችንን ፡ ቢያደርሱልን ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

ካለማወቅ ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ የሚደረሰው ፡ በትምህርት ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችን ፡ ከታቀዱት ፡ የልማት ፡ ፕሮግራሞች ፡ ቀደምትነት ፡ የሰጠነው ። ለትምህርት ፡ ነው ።

ትምህርት ፡ ታላቅ ፡ መሣሪያ ፡ ነው ፡ ለወደዱትም ፡ ጉዳይ ፡ ለማዋል ፡ የሚችል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ማናቸውም ፡ ተማሪ ፡ ለወገኑ ፡ ጥቅም ፡ እንጂ ፡ ለጉዳት ፡ እንዳያውለው ፡ ተመራምሮ ፡ ማወቅ ፡ የተገባ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ። በትምህርት ፡ ለመበልጸግ ፡ የሚደረገው ፡ ድካም ፡ ሁሉ ፡ በተገኘው ፡ እውቀት ፡ ራስን ፡ ብቻ ፡ ለመጥቀም ፡ ከሆነ ፡ እንዳልተማረ ፡ ሊቆጠር ፡ ይገበዋል ።

ኢትዮጵያ ፡ ከረጅም ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ ፡ የክርስትና ፡ ቅርስ ፡ በሰፊው ፡ የሚገኝበት ፡ አገር ፡ ናት ። ይህም ፡ ወደ ፡ እውነተኛ ፡ ትምህርት ፡ ለመድረስ ፡ የሚያስችል ፡ እድገት ፡ ትልቅ ፡ ኃይል ፡ ነው ። ሰው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሲኖር ፡ በመኖሩና ፡ በዕውቀቱ ፡ አገሩና ፡ ወገኑ ፡ የሚጠቀምበት ፡ ፈጣሪውም ፡ ደስ ፡ የሚሰኝበት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ትርፉ ፡ ምንድነው ።

የዓለም ፡ ሕዝብ ፡ በጠቅላላው ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰፊ ፡ ቤተሰብ ፡ ተቆጥሮ ፡ የዚሁ ፡ ቤተሰብ ፡ አባሎች ፡ የሆኑ ፡ እኩል ፡ ለሚጠቀሙበትና ፡ ለሚሻሻሉበት ፡ ዘዴ ፡ ካላሰቡና ፡ ካልተጣጣረ ፡ በፈጣሪው ፡ በኩል ፡ ያለበትን ፡ ኃላፊነት ፡ ካላወቀ ፡ በቀር ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ እውነተኛው ፡ ዕውቀት ፡ ደርሷል ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ።

በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለምትማሩ ፡ ተማሪዎች ፡ ባዲስ ፡ ዘመን ፡ የሚሰጠውን ፡ ትምህርት ፡ እየተማራችሁ ፡ ለአገራችሁ ፡ አገልግሎት ፡ በምትሰናዱበት ፡ ጊዜ ፡ የቀድሞውን ፡ የአባቶቻችሁን ፡ ባሕርይና ፡ ተግባር ፡ ባለ ፡ መዘንጋት ፡ የምትዘጋጁበትን ፡ ሥራ ፡ ፈጽማችሁ ፡ ወደፊት ፡ ለአገራችሁ ፡ ጠቃሚ ፡ እንድትሆኑ ፡ እንመኝላችኋለን ።

ትምህርት ፡ በዋጋ ፡ ሊገመት ፡ አይቻልም ። ለመማር ፡ ዕድል ፡ የሰጣችሁ ፡ ሁሉ ፡ ተጠቀሙበት ፡ እንጂ ፡ አታባክኑት ።

---



# 598

የኢራን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ ሚስተር ፡ ማሕሙድ ፡ ሳሌህ ፡ ሚያዝያ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. በ፫ ፡ ሰዓት ፡ በገነት ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ ንግግር ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

## ክቡር ፡ ሚኒስትር ።

ኢትዮጵያና ፡ ኢራን ፡ ያላቸው ፡ ግኑኝነት ፡ ከረጅም ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ስለሆነ ፡ ግርማዊ ፡ የኢራን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ይህንኑ ፡ ጸንቶ ፡ የቆየውን ፡ የተቀራረበ ፡ ወዳጅነት ፡ የበለጠ ፡ ለማጠንከር ፡ በማሰብ ፡ ክቡርነትዎን ፡ በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ አድርገው ፡ የሾሙበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ በደስታ ፡ ነው ።

ሁለቱን ፡ አገሮቻችንና ፡ ሌሎቹንም ፡ አገሮች ፡ የሚያጋጥሟቸው ፡ ታላላቅ ፡ ጉዳዮች ፡ ከመቸውም ፡ ይልቅ ፡ በዘመናችን ፡ እየተስፋፉና ፡ ፍሬ ፡ እያሳዩ ፡ በመሄድ ፡ ኅብረትና ፡ መደጋገፍ ፡ ሲፈጸሙ ፡ በማየታችን ፡ የሚሰማን ፡ ደስታ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይህን ፡ በጠነከረና ፡ በመልካም ፡ የተመሠረተውን ፡ ወዳጅነት ፡ ለማደርጀት ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ የእኛና ፡ የሚኒስትሮቻችን ፡ እርዳታ ፡ የማይጓደልብዎ ፡ መሆኑን ፡ ልናረጋግጥልዎ ፡ እንወዳለን ።

የተላኩበት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መልክት ፡ እንዲቃናልዎ ፡ እየተመኘን ፡ ለግርማዊ ፡ ሻህ ፡ ኢንሻህ ፡ ለግርማዊ ፡ እቴጌና ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተሰብ ፡ ደኅንነትና ፡ ደስታ ፡ ለታላቁና ፡ ለተከበሩ ፡ የኢራን ፡ ሕዝብ ፡ ልማትና ፡ እድገት ፡ ያለንን ፡ የልብ ፡ ምኞት ፡ እንዲገልጹልን ፡ እንጠይቅዎታለን ።

---

# 599

የሱዳን ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ክቡር ፡ ምስተር ፡ ከሊፋ ፡ አባስ ፡ ሚያዝያ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. በ፫ ፡ ሰዓት ፡ በገነት ፡ ልዑ

ል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ)የክቡር ፡ አምባሳደሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሆይ ።

በግርማዊነትዎ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዘንድ ፡ ከሱዳን ፡ ከፍተኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የሱዳን ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ሆኜ ፡ በመሾሜ ፡ ዛሬ ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤዬን ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ንጉሣዊ ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ ቀርቤ ፡ ለማበርከት ፡ ዕድል በማግኘቴ ፡ የሚሰማኝ ፡ ደስታና ፡ ክብር ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በአፍሪካ ፡ አህጉር ፡ ውስጥ ፡ የምትገኘው ፡ ታላቋና ፡ ጐረቤት ፡ እኅታችን ፡ በሆነችው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ የሀገሬ ፡ የሱዳን ፡ መንግሥት ፡ እንደራሴ ፡ ሆኜ ፡ በመሾሜ ፡ ምክንያት ፡ ለኔ ፡ ለራሴ ፡ የሚሰማኝ ፡ ክብርና ፡ ኩራት ፡ የተለየና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በኢትዮጵያ ፡ የሀገሬ ፡ መንግሥት ፡ እንደራሴ ፡ ሆኜ ፡ በመሾሜ ፡ ምክንያት ፡ ያለብኝ ፡ ሥራ ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ ታሪካዊ ፡ የሆነ ፡ የወዳጅነት ፡ ግኑኝነትና ፡ ዘለዓለማዊ ፡ የሆነውን ፡ የወንድማማችነት ፡ ፍቅር ፡ የጠነከረ ፡ ሆኖ ፡ እንዲገኝ ፡ ማድረግ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ወደፊት ፡ ስለሁለቱ ፡ ወዳጅ ፡ አገሮች ፡ የጋራ ፡ ጥቅምና ፡ መግባባት ፡ ያለውን ፡ ወዳጅነት ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ ለማጠንከር ፡ ለማስፋፋትና ፡ ለማደርጀት ፡ ነው ።

በታላቋ ፡ አገርዎ ፡ በቆየሁባቸው ፡ በነዚህ ፡ አጭር ፡ በሆኑት ፡ ጊዜያቶች ፡ ውስጥ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከፍ ፡ ወዳለው ፡ የሥልጣኔና ፡ የታላቅነት ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ በማናቸውም ፡ የኑሮ ድርጅት ፡ በኩል ፡ ያደረገቻቸውን ፡ እርምጃዎች ፡ ለማየትና ፡ ለመረዳት ፡ አስችለውኛል ።



አገሬ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ታላቅ ፡ ልቡና ፡ ውስጥ ፡ የምትገኝ ፡ በመሆንዋ ፡ የሚሰማት ፡ ደስታና ፡ ኩራት ፡ ክፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

ግርማዊነትዎ ፡ የሀገርዎን ፡ ሕዝብ ፡ ነፃ ፡ ለማውጣት ፡ መንግሥትዎን ፡ ነፃ ፡ በሆነ ፡ አቋም ፡ እንደገና ፡ ለመመሥረት ፡ ባደረጉት ፡ ትግል ተካፋይ ፡ የሆኑት ፡ የሱዳን ፡ ተወላጅ ፡ ወታደሮች ፡ ውለታቸው ፡ የማይረሳ መሆኑን ፡ በመግለጥ ፡ ባለፈው ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ለአንድ ፡ ጋዜጣ ፡ ወኪል ፡ የሰጡትን ፡ ንጉሣዊ ፡ መግለጫ ፡ በመስማታቸው ፡ የግርማዊነትዎን ፡ ልባዊ ፡ ፍቅርና ፡ ውለታ ፡ አዋቂነት ፡ በሰፊው ፡ ለማረጋገጥ ፡ ችሏል ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሆይ ።

ከፍ ፡ ያለ ፡ ኀላፊነት ፡ የተመላበትን ፡ ሥራዬን ፡ በማከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ የግርማዊነትዎና ፡ የመንግሥትዎ ፡ ደግነትና ፡ እርዳታ ፡ የማይለየኝ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ በጋለ ፡ ተስፋ ፡ ለመናገር ፡ ይፈቀድልኝ ፡ ይሆን ?

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሆይ ።

በከፍተኛው ፡ የሱዳን ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ በሱዳን ፡ ሬፐብሊክ ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለተወደደው ፡ ሕዝብዎ ፡ ያለውን ፡ ልባዊና ፡ እውነተኛ ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ ለማቅረብ ፡ እንዲፈቀዱልኝ ፡ በትህትና ፡ እለምናለሁ ።

* * *

ለ)የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ አምባሳደር ።

የኢትዮጵያና ፡ የሱዳን ፡ ሕዝቦች ፡ በወንድማማችነት ፡ ፍቅርና ፡ ስምምነት ፡ የኖሩባት ፡ ዘመን ፡ በብዙ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ሊቆጠር ፡ የሚቻል ነው ። ስለዚህ ፡ የታላቁና ፡ የተከበረው ፡ የሱዳን ፡ ሬፐብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ሁነው ፡ በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ስንቀበልዎ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ ነው ።

ሱዳኖች ፡ ወንድሞቻችን ፡ በኀዘናችንና ፡ በደስታችን ፡ ሳይለዩን ፡ ኀዘናችንና ፡ ደስታችንን ፡ እንደተካፈሉ ፡ እኛም ፡ በበኩላችን ፡ ሱዳን ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ታላቅ ፡ መንግሥት ፡ ሆኖ ፡ ሲቋቋምና ፡ እንደዚሁም ፡ አሁን ፡ በቅርቡ ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ አባል ፡ ሲሆን ፡ የተሰማን ፡ ደስታ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

ሁለቱ ፡ ሕዝቦች ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ የጋለ ፡ ዓላማ ፡ ለመድረስ ፡ አብረው ፡ ሲጣጣሩ ፡ ቆይተዋል ። ዛሬም ፡ እስጊ ፡ የሆነው ፡ የዓለም ፡ ሁኔታ ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ግብ ፡ የሚደርስበትን ፡ ዘዴ ፡ ለማግኘት ፡ በወንድማማችነትና ፡ በመተባበር ፡ ይደክማሉ ።

ክቡር ፡ አምባሳደር ፡ የመጡበትን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መልክት ፡ ይልቁንም፡ ሁለቱን ፡ ሕዝቦች ፡ በአንድነት ፡ ያስተሳሰራቸውን ፡ የተቀራረበ ፡ የወንድማማችነት ፡ ፍቅር ፡ በበለጠ ፡ ለማጠንከርና ፡ ለማደርጀት ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ የኛና ፡ የሚኒስትሮቻችን ፡ ሙሉ ፡ እርዳታ ፡ ከፍጹም ፡ መተባበር ፡ ጋር ፡ ስለማይጓደልብዎ ፡ ይህን ፡ እናረጋግጥልዎ ፡ ዘንድ ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ።

ክቡርነትዎ ፡ ለሱዳን ፡ ሬፐብሊክ ፡ ከፍተኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሰላምታችንን ፡ እንዲያደርሱልንና ፡ እንደዚሁም ፡ ለሱዳን ፡ ሕዝብ ፡ እድገትና ፡ ልማት ፡ ያለን ፡ የልብ ፡ ምኞት ፡ በምክር ፡ ቤቱ ፡ በኩል ፡ እንዲገለጽለት ፡ እንዲያደርጉ ፡ እንጠይቅዎታለን ።

---

# 600

የግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተመሠረተበትን ፡ ፳፭ኛ ፡ ዓመት ፡ የብር ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ለማክበር ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ሚያዝያ ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ዓ. ም. በ፱ ፡ ሰዓት ፡ በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ተገኝተው ፡ በዓሉን ፡ ካከበሩ ፡ በኋላ ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ዲሬክትሪስ ፡ ወይዘሮ ፡ ስንዱ ፡ ገብሩ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ)የወይዘሮ ፡ ስንዱ ፡ ገብሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።
ግርማዊት ፡ እቴጌ ።
ልዑላን ።



ክቡራን ፡ መኳንንትና ፡ ወይዛዝርት ።

ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ የሕዝባቸው ፡ ሥልጣኔ ፡ መሠረት ፡ እንዲኖረው፡ የሴቶች ፡ መማር ፡ ግድ ፡ የሚያስፈልግ፡ መሆኑን ፡ ተረድተው ፡ ያገራቸው ፡ ሴቶች ፡ እውቀት ፡ እንዲገበዩበት ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ግቢ ፡ ቆርጠው ፡ በግል ፡ ገንዘባቸው ፡ የግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የዛሬ ፡ ፳፭ ፡ ዓመት ፡ መሠረቱ ።

የግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ እጅ ፡ በከፈተላቸው ፡ በር ፡ ዛሬ ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ተማሪዎች ፡ በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ይገኛሉ ። ከሕፃናት ፡ ትምህርት ፡ (ከኪንደር ፡ ጋርተን ፡ ክፍል ፡) ሌላ ፡ የአስራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ትምህርት ፡ ይሰጥበታል ። የሁለተኛውን ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ እየጨረሱ ፡ ተማሪዎች ፡ ለማትሪኩሌሺን ፡ ፈተና ፡ መቅረብ ፡ ከጀመሩ ፡ አራተኛ ፡ ዓመት ፡ ነው ። በመሳሳትና ፡ በኩራት ፡ የምንመለከታቸው ፡ አሥር ፡ ሴቶች ፡ የዩኒቬርሲቲ ፡ ኰሌጅ ፡ ትምህርት ፡ ተካፋይ ፡ ሆነዋል ።

ግርማዊ ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሥልጣኔ ፡ ጐዳና ፡ በሚገባ ፡ ልትራመድ ፡ የምትችለው ፡ ሴቶች ፡ ከወንዶች ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ በትምህርት ፡ ሲገሰግሱ ፡ መሆኑን ፡ ተገንዝበው ፡ ይህንን ፡ የመጀመሪያ ፡ የሴቶች ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አበረከቱ ፡ በመሥራቿ ፡ በግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ለመጠራት ፡ የታደለው ፡ ይህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተጣለበትን ፡ አደራ ፡ ለመፈጸምና ፡ ለተሰጠው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስም ፡ ተገቢ ፡ ለመሆን ፡ ዛሬ ፡ የሚገኝበትን ፡ ደረጃ ፡ ይዟል ።

የግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የግርማዊ ፡ እቴጌ ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ የሥራ ፡ መሠረት ፡ ከጣሉበት ፡ ጊዜ ፡ ጋር ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ የሚራመድ ፡ ነው ፡ በሥራ ፡ ሠራዊት ፡ ታጅበው ፡ የንጉሥ ፡ ዘመናት ፡ በክብር ፡ ይጓዛሉ ።

እርምጃውን ፡ ያቋረጠው ፡ የጠላት ፡ ወረራና ፡ ፈተና ፡ መንግሥቱና ፡ ሕዝቡ ፡ በፈጸሙት ፡ ተጋድሎና ፡ መሥዋዕት ፡ የፈሰሰው ፡ ደም ፡ አንድነታችንን ፡ አጽንቶ ፡ ይገኛል ። በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የተፈጸመውን ፡ የተወጠነውን ፡ የታቀደውን ፡ የሥራ ፡ መጠን ፡ ለመገመት ፡ ዛሬ ፡ በጊዜው ፡ ላለነው ፡ ሰዎች ፡ አስቸጋሪ ፡ ይሆናል ።

ትልቁን ፡ ተራራ ፡ ከቅርብ ፡ ከግርጌው ፡ ከሚያየው ፡ ይልቅ ፡ ከሩቅ ፡ የሚመለከተው ፡ ነው ፡ በሙሉ ፡ የሚያየው ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡

ለትምህርት ፡ የፈጸሙትን ፤ እናንተ ፡ ባትናገሩ ፡ ድንጋዮች ፡ ይመሰክራሉ ፤ እንዳለው ፡ ጌታ ፡ በመናገሻ ፡ ከተማና ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ እንደ ፡ እንጉዳይ ፡ በቅለው ፡ የሚታዩት ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ብዛት ፡ ማማር ፡ ለትውልድ ፡ ይናገራሉ ፤ እነዚህ ፡ ከሚገልጹት ፡ በበለጠ ፡ ሊናገረው ፡ የሚቻለው ፡ የለም ።

በጠቅላላውም ፡ ሆነ ፡ በየመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ከተፈጸመው ፡ ይልቅ ፡ ያልተፈጸመውን ፤ ስለምናይ ፤ ወይም ፡ ሊፈጸም ፡ የምንመኘውን ፡ ለማየት፡ ስለምንመርጥ ፡ ተፈጽሞ ፡ ለሚገኘው ፡ ዋጋውን ፡ የነፈግነው ፡ ሲመስል ፡ በሌላው ፡ ጐን ፡ በተሠራው ፡ ያለመጥገብ ፡ የእድገት ፡ ምልክት ፡ የፕሮግሬ ፡ ሁሉ ፡ መነሻ ፡ ነው ።

የግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንደሌሎቹ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ የሚያሻሽለው ፡ እንዳለው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። አንዳንዱ ፡ በጊዜ ፡ ብቻ ፡ የሚደረስበት ፡ ሲሆን ፤ አንዳንድ ፡ አነስተኛ ፡ ምክንያቶችን ፡ በማስወገድ ፡ እርምጃውን ፡ ለማፋጠን ፡ እንደሚቻል ፡ የተገመተም ፡ አለ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ባለፈው ፡ ሁሉ፡ ለመርዳትና ፡ የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ ፈቃደኛም ፡ ቢሆን የተሸከመው ፡ ፍሬ ፡ እንደከበደው ፡ ዛፍ ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ቁጥር ፡ እየበረከተ ፤ ሥራው ፡ እየተስፋፋ ፡ በመሄድ ፤ የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ በበኩሉ ፡ ያለበትን ፡ ችግር ፡ በመገመት ፡ ትዕግሥት ፡ በተመላበት ፡ ተስፋ ፡ መጭውን ፡ እንመለከታለን ።

በትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ የተመደበውን ፡ ቋንቋና ፡ ጥበብ ፡ ብቻ ፡ ማስተማር ፡ በቂ ፡ አለመሆኑን ፡ በማስተማር ፡ ኃላፊነት ፡ ላለን ፡ ሁሉ ፡ እየጎላ ፡ ታይቶናል ። ትምህርት ፡ በዕውቀት ፡ ብልጫ ፡ ራስን ፡ ለመጥቀም ፡ ብቻ ፡ የሚሰጥ ፡ አይደለም ። ለራስ ፡ የሚያገኘው ፡ ለሌሎችም ፡ ከሚፈጽም ግዴታ ፡ ጋር ፡ ማመዛዘን ፡ አለበት ። ያንዱ ፡ ነፃነት ፡ የሌላውን ፡ ስለሚወሰን ፡ ወሰኑ ፡ መከበር ፡ አለበት ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፤ ነገሥታት ፡ አባቶቻቸው ፡ ከሕዝባቸው ፡ ጋር ፡ ያቆዩልንን ፡ ነፃነት ፡ የምንጠብቅበትን ፡ መሣሪያ ፡ ትምህርትን ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ በገፍ ፡ አቅርበውልናል ። ትምህርት ፡ ሰውነታችንን ፡ ክቡርና ፡ ነፃ ፡ የሚያደርግ ፡ ነው ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ማወቅ ፡ እው



ነት ፡ ነፃ ፡ ያደርጋችኋል ፡ ብሏል ፡ ከሌላው ፡ ትምህርት ፡ ጋር ፡ መማር ፡ ማስተማር ፡ የሚገባን ፡ ይኸንን ፡ ነው ።

ለትጋትና ፡ ለሥራ ፡ አርአያ ፡ ለትምህርት ፡ አባት ፡ ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ረጅም ፡ ዕድሜ ፡ ይስጥልን ፡ የርኅራኄና ፡ የትሕትና ፡ አርአያ ፡ የሆኑትን ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነንን ፡ አብሮ ፡ ያኑርልን ።

ዕድሜ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተሰብ ።

ኢትዮጵያ ፡ በነፃነት ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

❋ ❋ ❋

ለ)የግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ንግግር ።

ለአንድ ፡ አገር ፡ እድገትና ፡ ልማት ፡ ከትምህርት ፡ የተሻለ ፡ መድኃኒት ፡ አለመኖሩን ፡ በማመን ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መልካም ፡ ፈቃዳቸው ፡ ሆኖ ፡ ለወንዶች ፡ ልጆች ፡ በአደራጁላቸው ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሲጠቀሙ ፤ ወንዶች ፡ ተምረው ፡ ሴቶች ፡ ሳይማሩ ፡ ቢቀሩ ፡ የወንዶችና ፡ የሴቶች ፡ ኑሮ ፡ የተሟላ ፡ ሆኖ ፡ እንደማይገኝ ፡ በማወቅ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ተምሮ ፡ የአንዱ ፡ ክፍል ፡ አለመማር ፡ ላገሩ ፡ ከሚሰጠው ፡ ጥቅም ፡ የሚያስከትለው ፡ ጉዳት ፡ ይበልጣል ፡ ብለን ፡ በማሰብ ፡ ሴቶችም ፡ እንደ ፡ ወንዶች ፡ መማር ፡ ይገባቸዋል ፡ በማለት ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ ምሳሌ ፡ በመከተል ፡ የዛሬ ፡ ፳፫ ፡ ዓመት ፡ በግል ፡ ገንዘባችን ፡ ይህን ፡ ትምህርት ፡ ቤት፡ ከፈትን ።

ይህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሥራውን ፡ በመልካም ፡ አኳኋን ፡ ማራመድ፡ እንደጀመረ ፡ የጠላት ፡ ወረራ ፡ አቋርጦት ፡ ነበር ። በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ የወረራው ፡ ዘመን ፡ አልፎ ፡ እኛም ፡ በሥፍራችን ፡ ተመልሰን ፡ እንደተገኘን ፡ ተማሪ ፡ ቤቱ ፡ እንደገና ፡ ተቋቁሞ ፡ በጀመረው ፡ ዓላማ ፡ እንዲቀጥል ፡ አደረግን ። ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ በዚህ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ የሚሰጠው ፡ ትምህርት ፡ እየጨረሰ ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የደረሱና ፡ በመንግሥትም ሆነ ፡ በግል ፡ ሥራ ፡ እየገቡ ፡ የሚሠሩ ፡ ወጣት ፡ ሴቶች ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

ያገራችን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ የሚገባውን ፡ ትምህርት ፡ ካገኙ ፡ በአእምሯቸው ፡ ሥልነትና ፡ በዕውቀታቸው ፡ ከወንዶች ፡ ልጆች ፡ የማይሰንፉ ፡ መሆናቸው ፡ የታወቀ ፡ ስለሆነ ፡ ለአገራቸው ፡ ያለባቸውን ፡ ኃላፊነት ፡ አውቀው ፡ ከነሱ ፡ የሚጠበቀውን ፡ አገልግሎት ፡ በሰፊው ፡ ለማበርከት ፡

እንዲችሉ ፡ ተስፋችን ፡ ታላቅ ፡ ነው ።

የዛሬ ፡ ፳፭ ፡ ዓመት ፡ ይህ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ሲከፈት ፡ በውስጡ ፡ የነበሩት ፡ ተማሪዎች ፡ ከአምሳ ፡ የማይበልጡ ፡ ነበሩ ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ የትምህርትን ጣዕም ፡ አውቀው ፡ በትምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ የሚሳተፉ ፡ ቁጥራቸው ፡ ከሺህ፲፪ ፡ የማያንሱ ፡ ልጆች ፡ በማየታችን ፡ ደስታችን ፡ ታላቅ ፡ ነው ።

እግዚአብሔር ፡ ለዚህ ፡ አድርሶን ፡ ዛሬ ፡ ይህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተከፈተበትን ፡ ፳፭ኛውን ፡ ዓመት ፡ ለማክበር ፡ ስላበቃን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋናችንን ፡ እናቀርብለታለን ። የዚህን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እድገት ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ አድርጋ ፡ ችግሩንና ፡ ድካሙን ፡ ባለመመረር ፡ በፈጸመችው ፡ ሥራ ደስ ፡ ያሰኘችንን ፡ ዲሬክተሯንና ፡ ሴቶች ፡ መምህራኖችንም ፡ ጭምር ፡ ልናመሰግናቸው ፡ እንወዳለን ።

---

# 601

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፳፮ኛውን ፡ ዓመት ፡ የነፃነት ፡ በዓል ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ለጦር ፡ ኃይሎች ፡ መኰንኖች ፡ ወታደሮች ፡ ለሰላማዊ ፡ ፖሊስ ፡ መኰንኖችና ፡ ወታደሮች ፡ የተዘጋጀውን ፡ የአስራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ አገልግሎት ፡ የሜዳይ ፡ ሽልማት ፡ በየክፍሉ ፡ ሲሸልሙ ፡ የተናገሩት ፡ መሪ ፡ ቃል ።

በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለሙሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያቋቋም ነውን ፡ ያገልግሎት ፡ ሜዳይ ፡ ዛሬ ፡ እንድትሸለሙ ፡ ስናደርግ ፡ አገልግሎታችሁ ፡ ያልተዘነጋ ፡ መሆኑን ፡ የምታስታውሱበት ፡ ነው ። አገራቸውንና፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸውን ፡ በታማኝነትና ፡ በቅንነት ፡ ላገለገሉ ፡ ሁሉ ፡ የሚገባቸውን ፡ ያገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ ተገቢ ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ አስራ ዓምስት ፡ ዓመት ፡ ያለማቋረጥ ፡ በታማኝነት ፡ ላገለገሉ ፡ ለጦር ፡ ሠራዊት ፡ ለፖሊስ ፡ መኰንን ፡ እንደዚሁም ፡ ለጦር ፡ ሠራዊቶች ፡ ለፖሊስ ፡ የመደብነውን ፡ ሜዳይ ፡ ሽልማት ፡ እንድትቀበሉ ፡ ስንፈቅድ ፡ ተገቢውን፡ ነገር ፡ ማድረጋችን ፡ ነው ።

እናንተ ፡ አሁን ፡ በፊታችን ፡ ቀርባችሁ ፡ ይህን ፡ ሽልማት ፡ ለመቀበል ፡ ዕድላችሁ ፡ ቢመርጣችሁም ፡ ከአገልግሎታችሁ ፡ ጋራ ፡ በሥራችሁ፡



ምክንያት ፡ በየመደባቸው ፡ ተግባራቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ በየአውራጃው ፡ የሚገኙትን ፡ አገልጋዮቻችንን ፡ ሁሉ ፡ ሳንዘነጋ ፡ ይህ ፡ ለአገልግሎታቸው፡ መታሰቢያ ፡ የሆነው ፡ ሜዳይ ፡ በያለበት ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ስናዝ ፡ እነሱም ፡ እንደዚሁ ፡ ከፊታችን ፡ ቀርበው ፡ እንደሸለምናቸው ፡ ያህል ፡ እንቆጥረዋለን ።

በናንተ ፡ ላይ ፡ በጣልነው ፡ እምነት ፡ ተግታችሁ ፡ ስናያችሁ ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ ለወደፊቱ ፡ ይህን ፡ ለመሰለው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የተመረጣችሁና ፡ የተሰናዳችሁ ፡ ሆናችሁ ፡ እንድትገኙ ፡ ብርቱ ፡ መሆን ፡ አለባችሁ ።

የእድገታችሁን ፡ የዕድላችሁ ፡ ደጋፊ ፡ ሁኑ ፡ የመታመን ፡ ዋጋው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ ከልባችሁ ፡ አታጥፉ ።

---

# 602

፳፮ኛው ፡ ዓመት ፡ የነፃነት ፡ በዓል ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. እሁድ ፡ በአምስት ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሲከበር ፡ በሻምፓኝ ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርዋዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ)የክቡር ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ።

ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ድካም ፡ በግርማዊት ፡ ኃዘን ፡ ወደ ፡ ቀድሞው ፡ ነፃነታችን ፡ የተመለስንበትን ፡ የተቀደሰ ፡ ቀን ፡ ለማክበር ፡ በያመቱ ፡ ግርማዊነትዎንና ፡ ግርማዊትን ፡ ከዙፋናችሁ ፡ ላይ ፡ ስናያችሁ ፡ ደስታችን ፡ ዘወትር ፡ አዲስ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ተቀጥተን ፡ የተማርንበት ፡ ወድቀን ፡ የተነሣንበት ፡ ታሪካዊ ፡ ቀን ፡ የመለኮት ፡ ፍርድ ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ ኀይል ፡ እንዳለውና ፡ ነፃነት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ክብር ፡ ለሀገር ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ ኩራት ፡ መሆኑን ፡ ዘወትር ያስተምረናል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የአገርዎን ፡ የነፃነት ፡ ፋና ፡ ለሕዝብዎ ፡ ይዘው ፡ ከመጡ ፡ በኋላ ፡ እግ

ዚአብሔር ፡ ለሠራልዎ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ አይበቃም ፡ በማለት ፡ ሕግ ፡ የበላይ ፡ ገዥ ፡ እንዲሆን ፡ ሕገ ፡ መንግሥትዎን ፡ አሻሽለው ፡ እውነተኛውን ፡ የዴሞክራት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለሕዝብዎ ፡ ሰጡ ።

በዚህ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ አስተያየት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የሀገር ፡ ነፃነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ የተፈጥሮ ፡ መብት ፡ ስላገኘ ፡ ፍጹም፡ ነፃነት ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ሆነ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ላንድ ፡ ሕዝብ ፡ ነፃነትን ፡ ማግኘት ፡ ብቻ ፡ የሚበቃ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ተቀባዩ ፡ ሕዝብ ፡ የነፃነቱን ፡ ትርጉም ፡ ምን ፡ እንደሆነ፡ በጣም ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ።

ቮልቴር ፡ የሚባል ፡ የፈረንሳዊ ፡ የሕግ ፡ ሊቅ ፡ ነፃነት ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚገባው ፡ መብቱ ፡ ሲሆን ፡ የወገኑን ፡ ኑሮ ፡ ሳያበላሽና ፡ መብቱን ፡ ሳይደፍር ፡ በጥንቃቄ ፡ እንዲሠራበት ፡ ያስፈልጋል ፡ ይላል ።

ስለዚህ ፡ ነፃነት ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያስቀይም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ የሚያሳዝን ፡ ወገኑን ፡ የሚጐዳ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ከመብቱ ፡ ውጭ ፡ ነው ።

ነፃነትን ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ የአገርን ፡ ልምድና ፡ ሃይማኖትን ፡ ምግባርን ፡ መዳፈር ፡ መንቀፍ ፡ አይገባም ፡ በሰው ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ነፃነት ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ እንክርዳድ ፡ መዝራትና ፡ ሰውን ፡ በመጥፎ ፡ ትምህርት ፡ ማሳት ፡ ከሕግ ፡ የወጣ ፡ ዋና ፡ ጥፋት ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ መድኀኒታችን ፡ ወዮለት ፡ ለዚያ ፡ ለሰው ፡ ወንድሙን ፡ ለሚያስት ፡ የወፍጮ ፡ ድንጋይ ፡ ከአንገቱ ፡ ላይ ፡ አስሮ ፡ ከባሕር ፡ ውስጥ፡ ቢወድቅ ፡ ይሻለው ፡ ነበር ፡ ይላል ።

እንግዲህ ፡ ነገሬን ፡ ሳሳጥር ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በብዙ ፡ ደምና ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ የገዙዋትን ፡ ውድ ፡ ነፃነት ፡ ለቀላል ፡ ነገርና ፡ ለብልግና ፡ ልናውላት ፡ አይገባንምና ፡ የነፃነትን ፡ የመንፈስ ፡ ትርጉም ፡ በጣም ፡ ማጥናት ፡ ያስፈልጋል ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፤



ዕድሜ ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፤
ኢትዮጵያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ)የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

በእግዚአብሔር ፡ ኃይልና ፡ እርሱ ፡ በሠራው ፡ ፕላን ፡ ደካሞችን ፡ ሳይንቅ ፡ አሸንፎ ፡ እዚህ ፡ ተሰብስበን ፡ ይህንን ፡ ደስታ ፡ ለመካፈልና ፡ ለማክበር ፡ አሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ቀን ፡ ሰጥቶናል ።

አሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ትንሽ ፡ አይደለም ፤ በዚህ ፡ አሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመትም ፡ ውስጥ ፡ የተሠራው ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ አሥራ ፡ስድስት ፡ ዓመት ፡ ሳይሆን ፡ ከአሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ጀምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሪ ፡ ካደረገን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አስተዳደር ፡ ከመረጠን ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ በምናደርገው ፡ ማናቸውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ እንደየዕድሉ ፡ በምንሰጠውና ፡ በመራነው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ከና ፡ ጋር ፡ እንደተመረጠና ፡ እንደዚሁ ፡ ለሕዝባችን ፡ የምናስበውን ፡ ያህል ፡ ሁሉም ፡ በየበኩሉ ፡ እንዲረዳና ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በፓርላማ፡ ላይ ፡ ገልጠናል ።

አሁንም ፡ ደስታችንን ፡ ለሥጋችን ፡ የሚጥመውን ፡ ብቻ ፡ ደስታ ፡ ማድረግ ፡ ከእንስሳት ፡ ልዩነት ፡ የሌለው ፡ እንዳይሆን ፡ ደስታችን ፡ ሁሉ ፡ እኛም ፡ እራሳችን ፡ እናንተም ፡ በየመረጥናችሁ ፡ በየሰጠናችሁ ፡ ክፍል፡ ላይ ፡ ለሕዝቡ ፡ የሚጠቅመውንና ፡ ለሕዝቡ ፡ የሚያገለግለውን ፡ ነገር ፡ መሥራት ፡ ዋና ፡ ደስታ ፡ ነው ።

ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሕሊናው ፡ እንዳይወቅሰው ፡ ከኛ ፡ ገራ ፡ የተመረጠና ፡ ለኛ ፡ ሲያገለግል ፡ በእኛ ፡ አማካይነት ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አገሩንም ፡ ማገልገሉን ፡ መሆኑን ፡ አውቆ ፡ መሥራት ፡ እንዳለበት ፡ ማወቅ ፡ ነው ።

በአሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ከተሠራው ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የሚሰማን ፡ ደስታ ፡ ሕፃናቱም ፡ አዋቂውም ፡ ማናቸውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እንደተመኘንለት ፡ ለዕውቀቱና ፡ ለሃብቱ ፡ ሴሯሯጥ ፡ እናያለን ፤ በደ

ረጃውም ፡ ላይ ፡ ተሻምቶ ፡ ተዳርሶአልና ፡ ይኸንኑ ፡ ደረጃ ፡ እንዲወጣውና፡ ራሱንም ፡ አገሩንም ፡ ውለታውም ፡ እንዳይጠፋ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲመራው ፡ አደራውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንሰጣለን ። ፡ እዚህ ፡ ዓመት ፡ አድርሶ ፡ ሁላችሁንም ፡ አንድነት ፡ ሰብስቦ ፡ መላው ፡ ኢትዮጵያን ፡ እዚህም ፡ ያሉትን ፡ የሌሉትንም ፡ እዚህ ፡ ቀን ፡ ላደረሰን ፡ እግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

---

# 603

ልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍኑ ፡ ሐረር ፡ ግንቦት ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. እሁድ ፡ በመኪና ፡ አደጋ ፡ ስለሞቱ ፡ የቀብሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ግንቦት ፡ ፭ ፡ ቀን ፡ ሰኞ ፡ በመንበረ ፡ ፀባዖት ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተፈጸመ ። በቤተ ፡ መንግሥት ፡ እስከ ፡ ሣልሥቱ ፡ ድረስ ፡ ጽኑ ፡ ኀዘን ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሰ ሕዝባቸው ፡ ለተወዳጁ ፡ መስፍን ፡ ስላደረገው ፡ ከባድ ፡ ኀዘን ፡ ስሜታቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ በሣልስቱ ፡ ቀን ፡ ግንቦት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ረቡዕ ፡ የተናገሩት ፡ የማጽናኛና ፡ የምስጋና ፡ ቃል ።

በልጃችን ፡ በልዑል ፡ መኰንን ፡ ዕረፍት ፡ ምክንያት ፡ በደረሰብን ፡ ታላቅ ፡ ጉዳት ፡ የተወደደው ፡ ሕዝባችን ፡ በሙሉ ፡ ተማሪዎችም ፡ ሕፃናትም ፡ ሳይቀሩ ፡ የመሪር ፡ ኀዘናችን ፡ ተካፋይ ፡ ሆነው ፡ ጥልቅ ፡ ኀዘናቸውን ፡ ስለገለጹልን ፡ ዋጋቸውን ፡ አምላክ ፡ አይንሣ ።

እቴጌም ፡ እኔም ፡ ከልብ ፡ እናመሰግናለን ። ሕዝባችን ፡ በሙሉ ፡ ከልብ ኀዘናችንን ፡ በመካፈሉ ፡ ኀዘናችንን ፡ ይኸው ፡ ሊያስታግሰው ፡ ይችላል ።

በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ትምህርት ፡ እንዲያገኙ ፡ ያደረግናቸውም፡ ልጆች ፡ ወደቀብሩ ፡ ስንሄድ ፡ በየመንገዱ ፡ ላይ ፡ ባደረጉት ፡ ልቅሶና ፡ ኀዘን ፡ የሚገባቸውን ፡ ፈጽመዋል ። እርሱን ፡ በሥጋ ፡ ብንወልደው ፡ እነርሱን ፡ ደግሞ ፡ በትምህርት ፡ ወልደናቸዋልና ፡ ወንዶችም ፡ ሴቶችም ፡ ተማሪዎች ፡ ያለቀሱት ፡ ልቅሶ ፡ ለእኅት ፡ ለወንድም ፡ እንደሚለቀስ ፡ ነው ።

ከመኳንንቱ ፡ ከታላላቁም ፡ ሰው ፡ ከሀገር ፡ ውስጥና ፡ ከውጭ ፡ አገርም ፡ በቴሌግራም ፡ የሚደርሱን ፡ የኀዘን ፡ መግለጫ ፡ ቃሎች ፡ ያጽናኑናል ። የኛም ፡ የናንተም ፡ ልጅ ፡ እንደመሆኑ ፡ ኀዘናችን ፡ ኀዘናችሁ ፡ ሆኗል ።

ልጃችንን ፡ ልዑል ፡ መኰንንን ፡ የምንወደው ፡ በሁለት ፡ ምክንያት



ነው ።

፩ኛ፡ ልጃችን ፡ በመሆኑ ፡ የልጅም ፡ ሞት ፡ የሚያስከትለውን ፡ ጥልቅ፡ ኀዘንና ፡ በእኛም ፡ በእቴጌም ፡ በሚስቱም ፡ በልጆቹም ፡ በወንድሞቹም ፡ በእኅቶቹም ፡ ላይ ፡ የወደቀወን ፡ መሪር ፡ ኀዘን ፡ ወላድ ፡ ይፍረደው ።

፪ኛ ፡ ከሕፃንነቱ ፡ ጀምሮ ፡ ከአጠገባችን ፡ ሳይለይ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ በመላበት ፡ እርዳታውና ፡ አገልግሎቱም ፡ ብዙ ፡ ይጠቅመን ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነው። ይልቁንም ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜው ፡ በዘመቻው ፡ ጊዜ ፡ ከኛ ፡ አልለይም ፡ በማለት ፡ ደሴ ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ያሁሉ ፡ ቦምብ ፡ ሲወርድብን ፡ ከአደጋው ፡ ለማዳን ፡ ገላጋያችን ፡ ነበር ።

በስደትም ፡ ጊዜ ፡ የመጽናኛችን ፡ ምንጭ ፡ ነበር ። በወጣትነቱ ፡ ዘመን፡ ለአገራችን ፡ እድገት ፡ ለምናዘጋጀው ፡ ኢትዮጵያን ፡ የንቃትና ፡ የማስተዋል ፡ አርአያ ፡ ለመሆን ፡ የሚያደርገው ፡ ጥረት ፡ የምኞቱን ፡ ሥሩትና ፡ ቅን ፡ ሐሳብ ፡ የሚገልጽ ፡ ነበር ።

በፍርድ ፡ ወይም ፡ በኑሮ ፡ በመቸገር ፡ ለሚገኙት ፡ ጉዳያቸው ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ሳይሰለች ፡ የሚያመለክተን ፡ ትጉህ ፡ አሳሳቢያችን ፡ ነበር ። ይህንንም ፡ የተደረገላቸው ፡ የባለጉዳዮች ፡ ሕሊና ፡ ይቁጠረው ።

እንደዚህ ፡ ያለውንም ፡ ጉዳይ ፡ የሚያቀርብልን ፡ እንደወጣትነቱ ፡ መጠን ፡ ተድላና ፡ ጨዋታ ፡ ሳይፈልግ ፡ ከራት ፡ በኋላ ፡ ነበር ።

በዕድሜው ፡ ልጅ ፡ በአእምሮው ፡ አዋቂ ፡ ሁኖ ፡ በተለይ ፡ እንደ ፡ ሽማግሌ ፡ መካሪያችን ፡ ነበር ። እናቱ ፡ ጡት ፡ እኛ ፡ ጡጦ ፡ እያጠባን ፡ አሳደግነው ። መቅደማችንን ፡ እንጂ ፡ ይቀድመናል ፡ ብለን ፡ ሳናስብ ፡ ይህ ፡ አደጋ ፡ ደርሶን ፡ በግድ ፡ ተለያየን ።

ለልጆቹ ፡ ለሚስቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያዝዘንን ፡ ብናደርግም ፡ ለእርሱም ፡ ለእኛም ፡ ማን ፡ እንደርሱ ፡ ይሆነናል ። የሚያሳዝነን ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ ልጄ ፡ ስለሆነ ፡ ልጄ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አይበልጥብኝም ።

ሞት ፡ ለፍጡር ፡ ሁሉ ፡ የማይሻር ፡ የማይለወጥ ፡ ሕግ ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ በቸርነቱ ፡ የሕይወታችንን ፡ ዘመን ፡ ለማስጌጥ ፡ የሰጠንን ፡ ፍሬ ፡ ብዙ ፡ ደስታ ፡ አይተንበት ፡ እንደገና ፡ መልሶ ፡ ሲጠራው ፡ የርሱ ፡ ፈቃድ ፡ የተገለጠበትን ፡ ውሳኔ ፡ በትዕግሥት ፡ መቀበል ፡ ይገባናል ። ዛሬ፡

ሜልስቱ ፡ ሆነ ፡ ከእኛም ፡ እሩቀ ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይደረጋል ፡ እኛ ፡ ወደ ርሱ ፡ እንሄዳለን ፡ እንጂ ፡ እርሱ ፡ ወደኛ ፡ አይመጣም ። ሁላችንም ፡ ወደተ መረጥንበት ፡ አገልግሎት ፡ እንመለስ ፡ የምንጠቀመው ፡ ምንም ፡ የለም ። ራሱን ፡ ከሞት ፡ የሚያድን ፡ ሌላውን ፡ እንዴት ፡ ያድነዋል ። እግዚአብሔ ር ፡ ይህንን ፡ የፈሰሰውን ፡ እንባ ፡ ተቀብሎ ፡ ለሀገራችን ፡ ለሕዝባችን ፡ ደኅ ንነት ፡ ያድርግልን ። እንግዲህ ፡ ወደየሥራችሁ ፡ መሄድ ፡ ነው ።

# 604

ስለ ፡ ልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍን ፡ ሐረር ፡ ሞት ፡ ኀዘናቸውን ፡ ለመግለጥ ፡ ጠቅላይ ፡ አገረ ፡ ገዥዎች ፡ የአውራጃና ፡ የወረዳ ፡ ገዥዎች ፡ ወደ ፡ የተሾሙበት ፡ አገር ፡ ለመመለስ ፡ ግንቦት ፡ ፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ነገሥትና ፡ ከግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ሲሰናበቱ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ለአገረ ፡ ገዥዎቹ ፡ የተነገረ ፡ ቃል ።

የኀዘናችንን ፡ ከባድነት ፡ በማወቅ ፡ ሕዝቡ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ እየደረሰ ፡ ለማላቀስ ፡ ከየሥፍራው ፡ በመንዝና ፡ በመሰናዳት ፡ ላይ ፡ ይገኛል ፡ ይባ ላል ፡ እርግጥም ፡ መሆኑን ፡ ይኸው ፡ እዚሁ ፡ በደረሰው ፡ ብዛት ፡ ተረድነ ተነዋል ፡ ስለዚህ ፡ ለኀዘናችን ፡ ወሰን ፡ እንድናደርግለት ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ ሆነና ፡ ሕዝቡ ፡ በያለበት ፡ እናንተን ፡ አይቶ ፡ እንዲጽናና ፡ በማሰብ ፡ ሁላ ችሁ ፡ በየስፍራችሁ ፡ ተገኝታችሁ ፡ እኛን ፡ መስላችሁ ፡ እንድትቀበሉትና፡ እንድታረጋጉት ፡ ይሁን ።

# 605

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በተወዳጁ ፡ መስፍን ፡ በልዑል ፡ መኰንን ፡ ሞት ፡ ምክኒያት ፡ ኀዘኑን ፡ ለመግለጽ ፡ ከጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ የሚመ ጣው ፡ ሕዝባቸው ፡ በሚያደርገው ፡ ጉዞ ፡ ችግርና ፡ ጉዳት ፡ እንዳይደርስበት ፡ አስበው ፡ ግንቦት ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ለ፲፱ቱ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ያስተላለፉት ፡ መልእክት ።

በተወደደው ፡ ልጃችን ፡ በልዑል ፡ መኰንን ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ የደረ ሰብንን ፡ ከባድ ፡ ኀዘን ፡ ሕዝባችን ፡ የራሱ ፡ አድርጎ ፡ በሙሉ ፡ ፈቃድ ፡ ተካፋይ ፡ መሆኑን ፡ የገለጸበት ፡ ስሜት ፡ ልባችንን ፡ ነክቶታል ።



በደስታችን ፡ ጊዜ ፡ የደስታችን ፡ ተካፋ ፡ ሆኖ ፡ ካሳየው ፡ መልካም ፡ ምሳሌ ፡ ሌላ ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ በኀዘናችን ፡ ጊዜ ፡ ከልብ ፡ በገለጸው ፡ ጥልቅ ስሜት ፡ አሳቢያችንና ፡ ተቆርቋሪያችን ፡ መሆኑን ፡ አስረድቷል ።

በሩቅ ፡ ያለው ፡ ሕዝባችን ፡ በቅርብ ፡ ሆኖ ፡ ኀዘናችንን ፡ ለመካፈል ፡ መፈለጉንና ፡ ወደዚህ ፡ ጉዞ ፡ ለማድረግ ፡ ማሰቡን ፡ ስለሰማን ፡ ረጂም ፡ ጉዞ ፡ በማድረግ ፡ ድካም ፡ እንዳይደርስበትና ፡ የዕለት ፡ ተግባሩ ፡ እንዳይጓ ደልበት ፡ በማለት ፡ ሁሉም ፡ በያለበት ፡ ሆኖ ፡ ኀዘኑን ፡ እንዲገልጽ ፡ አድር ገናል ።

ሕዝባችን ፡ ኀዘኑን ፡ በሚገልጽበት ፡ ጊዜ ፡ እኛም ፡ በመካከሉ ፡ እንዳለን ፡ ያህል ፡ እንቆጥረዋለን ፡ የኀዘናችን ፡ ተካፋይ ፡ መሆኑን ፡ በሙ ሉ ፡ ልብ ፡ ለገለጸልን ፡ ለምንወደው ፡ ሕዝባችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ዋጋ ውን ፡ ይክፈለው ።

# 606

የኢትዮጵያና ፡ የኤርትራ ፡ አንድነት ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡ ግንቦት ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ለልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍን ፡ ሐረር ፡ ሐወልት ፡ ስለ ማቆም ፡ ጉዳይ ፡ አሳባቸውን ፡ ከገለጹ ፡ በኋላ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መ ልስ ።

ሀ/ የማኅበሩ አባሎች ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በደጉና ፡ በርኅሩኁ ፡ ልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍን ፡ ሐረር ፡ ልጅዎ ፡ አሳዛኝ ፡ ዕረፍት ፡ ከመላ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ጋር ፡ ተቀላ ቅለው ፡ በምር ፡ ያለቀሱ ፡ የኢትዮጵያና ፡ የኢርትሪያ ፡ አንድነት ፡ ማኅ በር ፡ አባሎች ፡ የሆኑት ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ዜጎችዎ ፡ የሚከተለውን ፡ ልመና ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ እንድናቀርብላቸው ፡ ልከውናል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍን ፡ ሐረር ፡ ደግና ፡ ርኅሩኅ ፡ መሆናቸው ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የታወቀ ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በድል ፡

አድራጊነት ፡ ወደ ፡ ዙፋንዎ ፡ እንደተመለሱ ፡ ልዑል ፡ መኰንን ፡ ወዲያው፡ መጀመሪያ ፡ ሆነው ፡ በ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከነፃነት ፡ የተራበውን ፡ የኤር ትራ ፡ ሕዝብ ፡ የጐበኙና ፡ የምሥራች ፡ ድምፅ ፡ በማሰማትና ፡ በግፍ ፡ ታስ ረው ፡ የነበሩትን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ወደሚገኙበት ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ ሄደው ፡ አይዞአችሁ ፡ ትፈታላችሁ ፡ ሲሉ ፡ ያጽናኑና ፡ በጊዜው ፡ ከነበሩት ፡ የእግሊዝ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጋር ፡ ተነጋግረው ፡ ብዙ ፡ እስረኞች ፡ ያስ ፈቱና ፡ የብዙዎችንም ፡ እስራት ፡ ያቃለሉ ፡ ስለሆኑ ፡ መላው ፡ የኤርትራ ፡ ሕዝብ ፡ ለዘላለም ፡ የማይዘነጋቸው ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ለልዑልነታቸው ፡ ማስታወሻ ፡ የሚሆን ፡ ሐውልትና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መታሰቢያ ፡ ለማቆም ፡ በኛ ፡ በጥቂቶቹ ፡ የኢትዮጵያና ፡ የኤርትራ ፡ አንድነት ፡ ማህበር ፡ አባሎች ፡ ዜጐችዎ ፡ የሚወሰን ፡ ብቻ ፡ ስንኳ ፡ ባይ ሆን ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ለኤርትርያ ፡ ሕዝብ ፡ የብርሃን ፡ ውጋጋን ፡ ለማ ሳየት ፡ በሄዱበት ፡ በደሴ ፡ መንገድ ፡ ሾላ ፡ በር ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ አነስተኛ ፡ ሐውልት ፡ ለማቆም ፡ የጋለ ፡ ፍላጎታችን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ክብር ፡ እንዲሰ ጠን ፡ አገልጋዮችዎ ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ትህትና ፡ ግርማዊነትዎን ፡ እንለምና ለን ።

* * *

ለ)ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ይህን ፡ ሐሳብ ፡ ስታቀርቡ ፡ ከልባችሁ ፡ መሆኑን ፡ በውነት ፡ እንረ ዳለን ። ልዑል ፡ መኰንን ፡ ስለ ፡ ኤርትራውያን ፡ የነበረው ፡ ሐሳብ ፡ ብዙ ፡ ነበር ። ምንም ፡ እሱ ፡ ቢያልፍ ፡ ሳናስታውሰው ፡ አንቀርም ። ስለአቀረባ ችሁት ፡ አሳብ ፡ እኛ ፡ ራሳችን ፡ አስበን ፡ አደራረጉን ፡ እናስታውቃችኋ ለን ።

## 607

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍነ ፡ ሐ ረር ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ ግንቦት ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ለሕዝባቸው ፡ የሰጡት ፡ ጠቃሚ ፡ ም ክር ።



የተወደደው ፡ ሕዝባችን ፡ በልጃችን ፡ በልዑል ፡ መኰንን ፡ ድንገተኛ፡ ሞት፡ ምክንያት ፡ የደረሰብንን ፡ ከባድ ፡ ኀዘን ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ለመካፈል ፡ ያሳየው ፡ አርአያ ፡ የኛን ፡ የእቴጌንና ፡ የቤተ ፡ ዘመዶችን ፡ ልብ ፡ ነክቶ ታል ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደተናገርነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በመላው ፡ ልጃችን ፡ ስለሆነ ፡ ባንድ ፡ ልጃችን ፡ ኀዘን ፡ አንለውጠውም ፡ ብለን ፡ ኀዘና ችንን ፡ ታግሠን ፡ ሥራችንን ፡ ስለጀመርን ፡ እንደዚሁም ፡ በየክፍሉ ፡ የሚ ገኙት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሥራቸውን ፡ እንዲቀጥሉ ፡ አዘን ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ እንደገና ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ለመናገር ፡ ያስገደደን ፡ የተወደደው ፡ ሕዝባችን ፡ የኀዘኑ ፡ ስሜት ፡ እየገፋው ፡ ከ፲፬ቱ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ የሚመጣው ፡ የሰው ፡ ቍጥር ፡ እየበዛ ፡ በመሄዱ ፡ ነው ።

ይልቁንም ፡ በባቡር ፡ በአውቶቡስና ፡ ባይሮፕላን ፡ ከሚመጣው ፡ በቀር ፡ መገናኛ ፡ ከሌለበት ፡ አገር ፡ በእግርና ፡ በፈረስ ፡ በበቅሎ ፡ ከሩቅ ፡ ስፍራ ፡ የሚደርሰውን ፡ ስንመለከት ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ለኛ ፡ ያለው ፡ ፍቅር ፡ ስሜት ፡ ደስ ፡ ሲያሰኘን ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ የድካሙን ፡ ብዛት ፡ ስናስብ ፡ እጅግ ፡ ያሳዝነናል ።

የተወደድኸው ፡ ሕዝባችን ።

ኀዘናችን ፡ ኀዘንህ ፡ ደስታችን ፡ ደስታህ ፡ እንደሆነ ፡ አይተናል ። ስለ ዚህ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የተናገርነውን ፡ እያስታወስን ፡ በኀዘናችን ፡ ምክን ያት ፡ ወደ ፡ መናገሻ ፡ ከተማችን ፡ ለመምጣት ፡ ሳትደክም ፡ ትልቁም ፡ ትንሹም ፡ ሹማምንትም ፡ ሆነ ፡ ባላገር ፡ ወደየተመረጥክበት ፡ ሥራና ፡ አገ ልግሎት ፡ እንድትመለስ ፡ ስንመክርህ ፡ ትእዛዝ ፡ ጭምር ፡ ነው ።

በልጃችን ፡ ላይ ፡ በደረሰው ፡ አደጋ ፡ ምክንያት ፡ የፈሰሰውን ፡ እንባ ፡ ለበረከት ፡ አድርጎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ሕዝቧን ፡ ይጠብቅ ።

## 608

በልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍነ ፡ ሐረር ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ መሪ ዎችና ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ በየጊዜው ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተላኩ ፡ የኀዘን ፡ መግለ ጫ ፡ ቴሌግራሞች ፡ እነዚህም ፡ በጋዜጣ ፡ ወጥተው ፡ የሚገኙት ፡ ናቸው ።

ከጃፓን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከግርማዊ ፡ ሂሮሂቶ ፡ የተላከ ።

እኔና ፡ ንግሥት ፡ የምናውቃቸው ፡ የልጅዎን ፡ የልዑል ፡ መኰንን ፡ የሐረር ፡ መስፍን ፡ ዕረፍት ፡ በመስማታችን ፡ እጅግ ፡ አድርገን ፡ አዝነናል ። ስለዚህ ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጥናችሁ ፡ በማለት ፡ ልባዊ ፡ የሆነ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነት ፡ መግለጫቻችንን ፡ እናቀርባለን ።

❋ ❋ ❋

ከእንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡ ከዳግማዊት ፡ ኤልሣቤጥ ፡ የተላከ ።

የመስፍኑ ፡ ሐረርን ፡ ሞት ፡ በታላቅ ፡ ኀዘን ፡ ሰማሁ ። እኔና ፡ ባለቤቴ፡ በልጅዎ ፡ ሞት ፡ ለደረሰብዎ ፡ ኀዘን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጥናዎ ፡ እያልን ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነት ፡ መግለጫችንን ፡ እንልካለን ።

❋ ❋ ❋

ከስዊድን ፡ ንጉሥ ፡ ከግርማዊ ፡ ጕስታቭ ፡ የተላከ ።

በልጅዎ ፡ ዕረፍት ፡ ምክንያት ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ኀዘን ፡ ስለተሰማን ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ይህን ፡ ልባዊ ፡ የሆነ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነታችን ፡ መግለጫ ፡ እንልካለን ።

❋ ❋ ❋

ከኒዘርላንድስ ፡ ንግሥት ፡ ከግርማዊ ፡ ጁልያናና ፡ ከባለቤታቸው ፡ ከልዑል ፡ ቤርናርድ ፡ የተላከ ።

በልጅዎ ፡ ድንገተኛ ፡ ሞት ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ኀዘን ፡ ተሰምቶናል ። ለግርማዊነትዎና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ልባዊ ፡ የሆነ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነታችንን ፡ መግለጫ ፡ እናቀርባለን ።

❋ ❋ ❋

ከኖርዌይ ፡ ንጉሥ ፡ ከግርማዊ ፡ ሐኮን ፡ የተላከ ።

የልጅዎን ፡ ዕረፍት ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጥልቃዊ ፡ ኀዘን ፡ ሰማን ። ለግርማዊነትዎ ፡ ልባዊ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነታችንን ፡ መግለጫ ፡ እንልካለን።



❋ ❋ ❋

ከዴንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ ከግርማዊ ፡ ፍሬድሪክ ፡ የተላከ ።

በደረሰብዎ ፡ ታላቅ ፡ ጉዳት ፡ ልባዊ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነታችንን ፡ መልእክት ፡ እንልካለን ።

❋ ❋ ❋

ከቤልጅግ ፡ ንጉሥ ፡ ከግርማዊ ፡ ቦድወ ፡ የተላከ ።

በግርማዊነትዎ ፡ ላይ ፡ የወደቀውን ፡ መሪር ፡ ኀዘን ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ ኀዘን ፡ ተሰምቶኛል ። ለግርማዊነትዎና ፡ ለልዑላን ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተሰብ ፡ ሁሉ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነውን ፡ የማጥናኛ ፡ ቃልና ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነቴን ፡ አቀርባለሁ ።

❋ ❋ ❋

ከፈረንሣይ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከክቡር ፡ ሙሴ ፡ ረኔ ፡ ኮቴ ፡ የተላከ ።

አሳዛኝ ፡ በሆነው ፡ በልዑል ፡ መኰንን ፡ መሥፍነ ፡ ሐረር ፡ ዕረፍት ፡ እጅግ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ኀዘን ፡ ተሰምቶኛል ። ግርማዊነትዎም ፡ ስለደረሰብዎት ፡ ኀዘን ፡ የማቀርበው ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነት ፡ መግለጫ ፡ መልእክት ፡ እንዲቀበሉኝ ፡ ስለምን ፡ በደረሰብዎ ፡ ጉዳት ፡ የተሰማኝን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ልባዊ ፡ ኀዘን ፡ እያረጋገጥሁ ፡ ነው ።

❋ ❋ ❋

ከዩጎስላቭ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከክቡር ፡ ማርሻል ፡ ቲቶ ፡ የተላከ ።

እጅግ ፡ አሳዛኝ ፡ የሆነውን ፡ የልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍነ ፡ ሐረርን ፡ ድንገተኛ ፡ ሞት ፡ በመስማቴ ፡ ልባዊ ፡ ኀዘን ፡ ተሰምቶኛል ። ግርማዊነትዎም ፡ የራሴንና ፡ የባለቤቴን ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነት ፡ መግለጫ ፡ እንዲቀበሉንና ፡ እንዲሁም ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተሰብ ፡ እንዲያስተላልፉልን ፡ እንለምናለን ።

❋ ❋ ❋

ከአሜሪካ ፡ ዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከክቡር ፡ ፕሬዚዳንት ፡ አይዘን ፡ ሐወር ፡ የተላከ ።

በልጅዎ ፡ በሐረር ፡ መስፍን ፡ ዕረፍት ፡ ለደረሰብዎ ፡ ኀዘን ፡ የማጥናኛ ፡ ቃሌንና ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነቴን ፡ መግለጫ ፡ አቀርባለሁ ።

* * *

ከሱዳን ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ከክቡር ፡ ምስተር ፡ አብደል ፡ ከሊፋ ፡ የተላከ ።

በመንግሥቴና ፡ በሱዳን ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ በመስፍኑ ፡ ሐረር ፡ ዕረፍት ፡ የተሰማኝን ፡ ጥልቅ ፡ ኀዘንና ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ የማጥናኛ ፡ መልእክት ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እልካለሁ ። በመስፍኑ ፡ ሞት የደረሰው ፡ ከባድ ፡ ኀዘን ፡ የወደቀው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ጽናቱን ፡ እንዲሰጣችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመለመን ፡ በሚገኘው ፡ በሱዳንም ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ነው ።

* * *

ከሕንድ ፡ ፕሬዚዴንት ፡ ከክቡር ፡ ራጀንድራ ፡ ፕራሳድ ፡ የተላከ ።

የሐረርን ፡ መስፍን ፡ ድንገተኛ ፡ አሳዛኝ ፡ ዕረፍት ፡ ወሬ ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ የኀዘን ፡ ፀፀት ፡ ተሰምቶኛል ። ለግርማዊነትዎ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌና ፡ ለሟቹ ፡ መስፍን ፡ ቤተሰብ ፡ በሕንድ ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ በራሴም ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ልባዊ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነት ፡ መግለጫ ፡ አቀርባለሁ ።

* * *

ከሕንድ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስት ፡ ከክቡር ፡ ጃዋህርላል ፡ ኔህሩ ፡ የተላከ ።

የሕንድን ፡ አገር ፡ የጎበኙትንና ፡ ብዙ ፡ ወዳጆች ፡ በአገራችን ፡ ያፈሩትን ፡ የሐረር ፡ መስፍን ፡ አሳዛኝ ፡ ዕረፍት ፡ ሰምቼ ፡ እጅግ ፡ አዝኛለሁ ።

ስለዚህ ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ለሐረር ፡ መስፍኒትና ፡ ለቤተ ፡ ሰባቸው ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነቴን ፡ መግለጫ ፡ እልካለሁ ።



* * *

ከግብጽ ፡ መንግሥት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከክቡር ፡ ኰሎኔል ፡ ጀማል ፡ አብደል ፡ ናስር ፡ የተላከ ።

በልጅዎ ፡ በልዑል ፡ መኰንን ፡ የሐረር ፡ መስፍን ፡ ላይ ፡ በደረሰው ፡ ያልታሰበ ፡ ድንገተኛ ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ እጅግ ፡ አዝኛለሁ ።

በራሴ ፡ በግብጽ ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ግርማዊነትዎ፡ ለደረሰብዎ ፡ ኀዘንና ፡ ጉዳት ፡ ልባዊ ፡ የሆነ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነቴን ፡ መግለጫ ፡ አቀርባለሁ ።

እግዚአብሔር ፡ የሟቹን ፡ ልዑል ፡ ነፍስ ፡ ይማር ፡ የግርማዊነትዎንም ፡ ዕድሜ ፡ ያርዝም ።

* * *

ከሜክሲኮ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከክቡር ፡ ሚስተር ፡ አዶልፍ ፡ ሩዊዝ ፡ ኮርቲኔስ ፡ የተላከ ።

የሐረሩን ፡ መስፍን ፡ የልዑል ፡ መኰንን ፡ አሳዛኝ ፡ ሞት ፡ በመስማታችን ፡ እጅግ ፡ አድርገን ፡ አዝነናል ። ስለዚህ ፡ በሜክሲኮ ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነት ፡ መግለጫ ፡ አቀርባለሁ ።

* * *

ከፖርቱጋል ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከክቡር ፡ ጀኔራል ፡ ክራይቬይሮ ፡ ሎፔስ ፡ የተላከ ።

የፖርቱጋል ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ ስለልዑል ፡ መኰንን ፡ የሐረር ፡ መስፍን ፡ ዕረፍት ፡ ልባዊ ፡ የሆነ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነት ፡ መግለጫ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ያቀርባል ።

* * *

ከስዊስ ፡ ኮንፌዴሬሽን ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከክቡር ፡ ሚስተር ፡ ሐንስ ፡ ስትሩውሊ ፡ የተላከ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ስዊዘርላንድን ፡ በጐበኙበት ፡ ጊዜ ፡ አብረው ፡ መጥተው ፡ የነበሩትን ፡ የልዑል ፡ መኰንንን ፡ ዕረፍት ፡ በመስማቴ ፡ እጅግ ፡ አዝኛለሁ ። ለግርማዊነትዎ ፡ የፌዴራሉን ፡ ምክር ፡ ቤትና ፡ የራሴን ፡ ጥልቅ፡ የሆነ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነት ፡ መግለጫ ፡ መልእክት ፡ ስልክ ፡ እንዲቀበሉኝ ፡ በመለመን ፡ ነው ።

* * *

ከኢጣልያ ፡ ሪፐብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከክቡር ፡ ሲኞር ፡ ግሮንኪ ፡ የተላከ ።

በልዑል ፡ ልጅዎ ፡ ድንገተኛ ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ በግርማዊነትዎና ፡ በልዑላን ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተሰብ ፡ ላይ ፡ ስለወደቀው ፡ ከባድ ፡ ኀዘን ፡ የማጥናኛ ፡ ቃሌን ፡ አቀርባለሁ ።

* * *

ከእሥራኤል ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ከክቡር ፡ ሚስተር ፡ ዴቪድ ፡ ቤን ፡ ጐሪዮን ፡ የተላከ ።

የልጅዎን ፡ የሐረር ፡ መስፍንን ፡ ዕረፍት ፡ ወሬ ፡ በመስማቴ ፡ እጅግ ፡ አድርጌ ፡ አዝኛለሁ ፡ የኔም ፡ ሐሳብ ፡ ከግርማዊነትዎና ፡ ከግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ከሐረር ፡ መስፍኒትና ፡ ከቤተሰባቸውም ፡ ጋር ፡ ነው ። በራሴና ፡ በእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ የማቀርብልዎትን ፡ ልባዊ ፡ የሆነ ፡ የማጣናኛ ፡ መልእክቴን ፡ እባክዎን ፡ ይቀበሉኝ ።

* * *

ከእስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከክቡር ፡ ጄኔራል ፡ ፍራንኮ ፡ የተላከ ።

በተወዳጅ ፡ ልጅዎ ፡ ሞት ፡ ለደረሰብዎ ፡ ኀዘን ፡ ይህንን ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ የማጥናኛ ፡ ቃልና ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይ ፡ መሆናችንን ፡ የሚገልጽ ፡ መልእክት ፡ እንዲቀበሉን ፡ እንለምናለን ።

* * *

ከበርማ ፡ አንድነት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከክቡር ፡ ዊን ፡ ማውንግ ፡ የተላከ ።

የልዑል ፡ መኰንን ፡ የሐረር ፡ መስፍን ፡ ድንገተኛ ፡ የሆነ ፡ አሳዛኝ ፡ ሞት ፡ ወሬ ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ አሳዝኖናልና ፡ ስለዚህ ፡ በመንግሥቱና ፡ በበርማ ፡ አንድነት ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ለንጉሣውያን ፡ ቤተሰብና ፡ ለአገሪቱ ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ የማጥናኛ ፡ መልእክቴን ፡ አቀርባለሁ ።

* * *

ከጃፓን ፡ አልጋወራሽ ፡ ከልዑል ፡ አኪሂቶ ፡ የተላከ ።



የሐረሩን ፡ መስፍን ፡ የልዑል ፡ መኰንንን ፡ ድንገተኛ ፡ ዕረፍት ፡ ስሰማ ፡ በጣም ፡ አዘንኩ ፡ ስለዚህ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ከደረሰብዎ ፡ ኀዘን ፡ ተካፋይ ፡ መሆኔን ፡ ፈጥኜ ፡ እገልጻለሁ ።

* * *

ከጃፓን ፡ መስፍን ፡ ከልዑል ፡ ታካማትሱ ፡ የተላከ ።

በልዕልት ፡ ቺቺቡ ፡ በልዕልት ፡ ታካማትሱ ፡ በልዕልት ፡ ሚካስና ፡ በራሴ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ላይ ፡ በደረሰው ፡ ከባድ ፡ ኀዘን ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነታችንን ፡ የሚገልጽ ፡ መልእክት ፡ ፈጥኜ ፡ አቀርባለሁ ።

* * *

ከአሜሪካን ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከክቡር ፡ ሚስተር ፡ ሪቻርድስ ፡ ኒክሰን ፡ የተላከ ።

ባለፈው ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አገርዎን ፡ በጐበኘሁበት ፡ ሰዓት ፡ የተዋወቅኋቸውን ፡ የሐረርን ፡ መስፍን ፡ ዕረፍት ፡ ስሰማ ፡ ጥልቅ ፡ ኀዘን ፡ ተሰምቶኛል ።

የልዑልነታቸው ፡ ዕረፍት ፡ በግርማዊነትዎና ፡ በግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ጉዳት ፡ ያስከተለ ፡ መሆኑን ፡ ተረድቻለሁ ። ስለዚህ ፡ እኔና ፡ ባለቤቴ ፡ ሚስስ ፡ ኒክሰን ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነታችንን ፡ መግለጫ ፡ እናቀርባለን ።

* * *

ከሱዳን ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ (ሱፕሪም ፡ ካውንስል) ፕሬዚዳንት ፡ ከክቡር ፡ አሕመድ ፡ መሐመድ ፡ ያሲን ፡ የተላከ ።

በልዑል ፡ መኰንን ፡ ዕረፍት ፡ ምክንያት ፡ ስለደረሰው ፡ ከባድ ፡ ኀዘን፡ በራሴና ፡ በሱዳን ፡ ሪፐብሊክ ፡ ከፍተኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ከልብ ፡ የሆነውን ፡ ከባድ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነት ፡ መግለጫ ፡ መልእክት ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ስልክ ፡ እጅግ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ኀዘን ፡ የተሰማኝ ፡ መሆኑን ፡ እያረጋገጥሁ ፡ ነው ።

ልዑልነታቸውን ፡ የምናውቃቸውና ፡ እጅግ ፡ የምናፈቅራቸው ፡ ሁለ በመሞታቸው ፡ እጅግ ፡ እናዝናለን ፡ በዚህ ፡ አሳዛኝ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ጥንካሬ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ እንለ ምናለን ።

❋ ❋ ❋

ከአሜሪካን ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፡ ከክቡር ፡ ሚስተር ፡ ጆን ፡ ፎስተር ፡ ደለስ ፡ የተላከ ።

ግርማዊነትዎና ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ በልጃችሁ ፡ እረፍት ፡ በደረሰባ ችሁ ፡ ኀዘን ፡ እኔና ፡ ባለቤቴ ፡ ሚስስ ፡ ደለስ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነታችንን ፡ እንገልጻለን ።

❋ ❋ ❋

ከጃፓን ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፡ ከክቡር ፡ ሚስተር ፡ ሬንዞ ፡ ሶዎዳር ፡ የተላከ ።

በልዑል ፡ መኰንን ፡ የሐረር ፡ መስፍን ፡ ድንገተኛ ፡ ዕረፍት ፡ የተሰ ማኝ ፡ ኀዘን ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። የኀዘን ፡ ተካፋይነቴንም ፡ ከልብ ፡ በመግለጽ ፡ ለግርማዊነታቸውና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ የማጥናኛ ፡ ቃሌን፡ እንዲነግሩልኝ ፡ እጠይቅዎታለሁ ።

❋ ❋ ❋

ከሱዳን ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፡ ከክቡር ፡ ሚስተር ፡ መሐመድ ፡ አሕመድ ፡ የተላከ ።

በልዑል ፡ መኰንን ፡ የሐረር ፡ መስፍን ፡ አሳዛኝ ፡ ዕረፍት ፡ የተሰማ ኝን ፡ ኀዘን ፡ መግለጫና ፡ የማጥናኛ ፡ መልክቴን ፡ እባክዎ ፡ ክቡርነትዎ ፡ ይቀበሉኝ ፡ ሁላችንም ፡ በምናውቃቸውና ፡ እጅግ ፡ በምንወዳቸው ፡ ልዑል ሞት ፡ የተሰማኝ ፡ ኀዘን ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

❋ ❋ ❋

ከእስፓኝ ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፡ ከክቡር ፡ ሲኞር ፡ ፌርናንዶ ፡ ካስቴላ ፡ የተላከ ።

የእስፓኝ ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ የሐረሩን ፡ መስፍን ፡ የልዑል ፡ መኰንን ፡ ዕረፍትና ፡ በንጉሣዊ ፡ ቤተሰብ ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡



ከባድ ፡ ጉዳት ፡ በታላቅ ፡ ኀዘን ፡ ሰምቶታል ። ስለዚህ ፡ ለግርማዊና ፡ ለግር ማዊት ፡ እቴጌ ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ የማጽናኛ ፡ መልእክታችንን ፡ እንዲያስተ ላልፉልን ፡ እንለምንዎታለን ።

❋ ❋ ❋

ከሱዳን ፡ የመንፈሳዊና ፡ የፖለቲካ ፡ መሪ ፡ ከአብድል ፡ ኤል ፡ ማሕዲ ፡ የተላከ ።

የአገራቸው ፡ መልክተኛ ፡ ሆነው ፡ በቅርቡ ፡ ጊዜ ፡ የሱዳንን ፡ አገር ፡ ጐብኝተው ፡ የነበሩትን ፡ የግርማዊነትዎን ፡ ልጅ ፡ የልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍነ ፡ ሐረርን ፡ ሞት ፡ በሰማን ፡ ጊዜ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ኀዘንና ፡ ጸጸት ፡ ተሰምቶናል ።

በዚህም ፡ መሪር ፡ ኀዘን ፡ ምክንያት ፡ ከልቤ ፡ የመነጨውን ፡ የማጥ ናኛ ፡ ቃል ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ እንዲሁም ፡ ለል ዑላን ፡ ቤተሰቦች ፡ አቀርባለሁ ።

እግዚአብሔር ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ እረጅም ፡ የሆነ ፡ ዕድሜ ፡ እንዲሰጥ ዎትና ፡ የሚቹ ፡ ልዑል ፡ ልጅዎንም ፡ ነፍስ ፡ ይማር ፡ እያልኩ ፡ ጸሎት ፡ አ ደርጋለሁ ።

❋ ❋ ❋

ከሱዳን ፡ ሕዝብ ፡ አንድነት ፡ ክፍል ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከክቡር ፡ እስማኤል ፡ አልዛሐሪ ፡ የተላከ ።

የተወዳጅ ፡ ልጅዎ ፡ የሐረር ፡ መስፍን ፡ ዕረፍት ፡ አሳዛኝ ፡ ወሬ ፡ ልባ ችንን ፡ ሰብሮታል ። ለግርማዊነትዎ ፡ ለመላው ፡ ለንጉሣውያን ፡ ቤተሰብ ፡ ከባዱን ፡ ኀዘን ፡ የምትችሉበት ፡ ትዕግሥት ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲሰጣ ችሁ ፡ እንጸልያለን ። ግርማዊነትዎም ፡ የኀዘን ፡ መግለጫችንን ፡ እንዲቀ በሉን ፡ እንለምናለን ።

❋ ❋ ❋

በትራስትሽፕ ፡ ከሚተዳደረው ፡ የሱማሌ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ከክቡር ፡ ሚስተር ፡ አቡዱላሂ ፡ ኢሳ ፡ የተላከ ።

በኔና ፡ በሱማሌ ፡ መንግሥት ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ በልዑል ፡ መኰንን ፡ ዕረ ፍት ፡ ምክንያት ፡ ለደረሰብዎት ፡ ኀዘን ፡ የማጥናኛ ፡ መልእክቴን ፡ አቀር

ባለሁ ።

❊ ❊ ❊

በኢትዮጵያ ፡ ከሚገኙት ፡ የሱዳን ፡ አምባሳደር ፡ ከክቡር ፡ ሚስተር ፡ አባስ ፡ ኢሎቢይድ ፡ የተላከ ።

በተወዳጁ ፡ በልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍን ፡ ሐረር ፡ ድንገተኛ ፡ ሞት ፡ የተሰማንን ፡ መሪር ፡ ኀዘንና ፡ ፀፀት ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ለልዑላን ፡ ቤተሰቦቻቸው ፡ እናቀርባለን ።

ልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍን ፡ ሐረር ፡ የሱዳን ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ፡ ታላቅ ፡ ወዳጅ ፡ ስለነበሩ ፡ የልዑልነታቸው ፡ ሞት ፡ ያስከተለውን ፡ ኀዘን ፡ የሱዳን ፡ ሬፑብሊክ ፡ ተካፋይ ፡ መሆኑን ፡ ይገልጣል ።

እግዚአብሔር ፡ ነፍሳቸውን ፡ ይማር ።

❊ ❊ ❊

ከግብጽ ፡ የፋዩም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ከብፁዕ ፡ አቡነ ፡ አትናስዮስ ፡ የተላከ ።

የልዑልነታቸውን ፡ ዕረፍት ፡ በሰማን ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ኀዘ ን ፡ ተሰምቶናል ። ይህንንም ፡ በኦርቶዶክስ ፡ ቤተክርስቲያናችን ፡ ላይ ፡ የደ ረሰውን ፡ ጉዳት ፡ በመመልከት ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተሰብና ፡ ለመላው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ትዕግሥቱንና ፡ ጽና ቱን ፡ እንዲሰጣችሁና ፡ እንዲሁም ፡ ለታላቋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የግርማዊነትዎ፡ ሕይወት ፡ እንዲጠበቅ ፡ በማለት ፡ ለፈጣሪያችን ፡ ጸሎት ፡ በማቅረብ ፡ ላይ፡ ነኝ ።

❊ ❊ ❊

ከካርቱም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ከብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ የተላከ ።

ትህትና ፡ የተመላውን ፡ ጸሎቴን ፡ ከማድረጌ ፡ በላይ ፡ ለግርማዊነት ዎና ፡ ለንጉሣዊያን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነቴን ፡ መግለጫ ፡ አቀርባለሁ ።

❊ ❊ ❊

ከግሪክ ፡ ፓትሪያሪክ ፡ ከብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ክርስቶፎሮስ ፡ የተላከ ።



በግርማዊነትዎና ፡ በንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብዎ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ ታ ላቅ ፡ ኀዘን ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፡ የሚቹ፡ መስፍን ፡ ነፍስ ፡ በሰላም ፡ እንድ ታርፍና ፡ ለግርማዊነትዎም ፡ መጥናኛ ፡ ይሰጥዎ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን፡ በጸሎት ፡ እለምናለሁ ።

❊ ❊ ❊

ከምዕራብ ፡ ቤንጋል ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ከክቡር ፡ ፓድማጅያ ፡ ናይዱ ፡ የተላከ ።

የወደቀብዎትን ፡ መሪር ፡ ኀዘን ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፡ በጣም ፡ ጥልቅ፡ የሆነውን ፡ የማጥናኛ ፡ ቃሌን ፡ እንዲቀበሉኝ ፡ እለምናለሁ ።

❊ ❊ ❊

ከአሜሪካን ፡ ከጆን ፡ ሮክፌለር ፡ የተላከ ።

የደረሰብዎትን ፡ መሪር ፡ ኀዘን ፡ ስሰማ ፡ ኀዘኔ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሆ ነ ፡ ስለዚህ ፡ እኔና ፡ ባለቤቴ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነታችንን ፡ ስ ሜት ፡ እንገልጻለን ።

❊ ❊ ❊

ከቤልግሬድ ፡ ከተማ ፡ ከንቲባ ፡ የተላከ ።

በቤልግሬድ ፡ ከተማ ፡ ሕዝብና ፡ በራሴም ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ በልጅዎ ፡ በልዑል ፡ መኰንን ፡ የሐረር ፡ መስፍን ፡ ሞት ፡ ለደረሰብዎት ፡ ከባድ ፡ ኀዘን ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ የኀዘን ፡ ስሜታችንን ፡ ለመግለጽ ፡ እመኛለሁ ።

❊ ❊ ❊

ከፓኪስታን ፡ ከክቡር ፡ አጋካን ፡ የተላከ ።

የልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍን ፡ ሐረርን ፡ አሳዛኝ ፡ ሞት ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ ጥልቅ ፡ ኀዘን ፡ ተሰምቶኛል ። ስለዚህም ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነትና ማጥናኛ ፡ ቃሌን ፡ እንዲቀበሉኝ ፡ እለምና ለሁ ።

* * *

ከሚስተር ፡ ኤድዊን ፡ ቸፕማን ፡ አንድሪው ፡ የተላከ ።

እጅግ ፡ በመረረ ፡ ኀዘን ፡ ላይ ፡ ሆኜ ፡ በባለቤቴና ፡ በራሴ ፡ ስም ፡ ስለደረሰብዎት ፡ ከባድ ፡ ኀዘን ፡ ጥልቅ ፡ ስሜት ፡ ያለበትን ፡ የማጥናኛ ፡ ቃልና ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነት ፡ መግለጫ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ እንዲቀበሉኝ ፡ አቀርባለሁ ።

* * *

ከሚስተር ፡ ሳውሪክ ፡ ጎትዝዎርድ ፡ የተላከ ።

ወዳጃችን ፡ በሆኑት ፡ በተወዳጁ ፡ ልጅዎ ፡ በልዑል ፡ መኰንን ፡ ሞት፡ ምክንያት ፡ በግርማዊነትዎና ፡ በንጉሣዊ ፡ ቤተሰብዎ ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ ከባድ ፡ ኀዘን ፡ ከልብ ፡ ተካፋይ ፡ መሆናችንን ፡ እንገልጻለን ።

* * *

ከአሜሪካ ፡ ከዶክተር ፡ ሳይመንሰን ፡ የተላከ ።

ሚስስ ፡ ሳይመንሰንና ፡ እኔ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌና ፡ ለልዑል ፡ መኰንን ፡ የሐረር ፡ መስፍን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይነታችንን ፡ መግለጫ ፡ እናቀርባለን ።

* * *

በሕንድ ፡ ካሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምባሳደር ፡ ከልዑል ፡ እራስ ፡ እምሩ ፡ የተላከ ።

በልዑል ፡ መኰንን ፡ ላይ ፡ በደረሰው ፡ አደጋ ፡ ሁላችንም ፡ አዝነናል ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጥናዎ ።

* * *

በምዕራብ ፡ ጀርመን ፡ ካሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምባሳደር ፡ ከክቡር ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኤፍሬም የተወልደ ፡ መድኅን ፡ የተላከ ።

የወደቀብን ፡ ታላቅ ፡ አደጋ ፡ ቴሌግራም ደርሶን ፡ ለመንግሥቱ ፡ በኦፊሺያል ፡ አስታውቀናል ።

ለግርማዊና ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ለልዑላን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ የከባድ ፡ ጥልቅ ፡ ኀዘን ፡ ተካፋይነታችንን ፡ እንገልጻለን ።



* * *

በሎንዶን ፡ ካሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምባሳደር ፡ ከክቡር ፡ አቶ ፡ አማኑኤል ፡ አብርሃም ፡ የተላከ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ፡ የተወደዱትን ፡ ልጅዎን ፡ የልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍን ፡ ሐረርን ፡ ድንገተኛ ፡ ዕረፍት ፡ ሰምተን ፡ እዚህ ፡ ያለን ፡ አገልጋዮችዎ፡ እጅግ ፡ አዝነናል ።

አምላክ ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ለመላው ፡ ንጉሣዊ ቤተ ፡ ሰብም ፡ መጽናናቱን ፡ እንዲሰጥ ፡ ጸሎታችን ፡ መሆኑን ፡ በታላቅ ፡ ትህትና ፡ እንገልጻለን ።

* * *

በሞስኮ ፡ ካሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምባሳደር ፡ ከክቡር ፡ አቶ ፡ ዘውዴ ፡ ገብረሕይወት ፡ የተላከ ።

በተወደዱት ፡ በልዑል ፡ መኰንን ፡ ዕረፍት ፡ ምክንያት ፡ በደረሰው ፡ ከባድና ፡ መራር ፡ የሆነ ፡ ኀዘን ፡ ተካፋይነታችንን ፡ እየገለጽሁ ፡ ቸር ፡ አምላክ ፡ የሚያጽናናውን ፡ መላክ ፡ ይላክልዎ ፡ በማለት ፡ የኀዘን ፡ መግለጫዬን ፡ አቀርባለሁ ።

* * *

በካርቱም ፡ ካሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምባሳደር ፡ ከክቡር ፡ አቶ ፡ መለሰ ፡ አንዶም ፡ የተላከ ።

የልዑል ፡ ጌታዬን ፡ መስፍነ ፡ ሐረርን ፡ ድንገተኛና ፡ አሳዛኝ ፡ ዕረፍት ፡ በመስማቴ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የመረረ ፡ ኀዘን ፡ ተሰምቶኛል ። ይህ ፡ ኀዘን፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ለሚገኙት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጆች ፡ ስለሆነ ፡ የደረሰብንን ፡ መሪርና ፡ ከባድ ፡ ኀዘን ፡ በተሰበረ ፡ ልባችን ፡ ስንቀበል ፡ ሁሉን ፡ የሚችል ፡ ቸር ፡ አምላክ ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብዎ ፡ ጥናት ፡ እንዲሰጥ ፡ ጸሎቴ ፡ ነው ፡ ስል ፡ ከባድና ፡ መራራ ፡ የሆነ ኀዘኔን ፡ በትህትና ፡ እገልጻለሁ ።

* * *

በቤልግራድ ፡ ካሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምባሳደር ፡ ከክቡር ፡ አቶ ገብረመስቀል ፡ ክፍለ ፡ እግዚእ ፡ የተላከ ።

በልዑል ፡ ጌታዬ ፡ መስፍነ ፡ ሐረር፡ ድንገተኛ ፡ ዕረፍት ፡ ምክንያት ፡

በግርማዊነታቸው ፡ ላይ ፡ ስለደረሰው ፡ ከባድ ፡ ኀዘን ፡ ራሴና ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቼ ፡ ሁሉ ፡ የተሰማንን ፡ ትልቅ ፡ ኀዘን ፡ እንዲገልጡልን ፡ በማክበር ፡ እለምናለሁ ።

* * *

በካይሮ ፡ ካሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምባሳደር ፡ ከክቡር ፡ ባላምበራስ ፡ አሸብር ፡ ገብረሕይወት ፡ የተላከ ።

የልዑል ፡ ጌታዬ ፡ መስፍን ፡ ሐረር ፡ ዕረፍት ፡ ምትክ ፡ የሌለው ፡ የአገር ፡ ጉዳት ፡ በካይሮ ፡ የምንገኘው ፡ ሕዝቦችዎ ፡ የአባትነትዎን ፡ ጥኑ ፡ ኀዘንና ፡ የጋራችንን ፡ ጉዳት ፡ በጥልቅ ፡ ሐሊና ፡ ተካፋዮች ፡ ነን ።

* * *

በስዊድን ፡ ካሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሚኒስትር ፡ ከክቡር ፡ አቶ ፡ ተድላ ፡ ባይሩ ፡ የተላከ ።

በልዑል ፡ መስፍን ፡ ሐረር ፡ አደገኛ ፡ ዕረፍት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ከባድና ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ኀዘን ፡ ሲወርድበት ፡ በግርማዊነትዎና ፡ በግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ በንጉሣውያን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ላይ ፡ የወረደውን ፡ ኀዘን፡ የሰው ፡ አእምሮ ፡ ሊገምተው ፡ የማይችል ፡ ነው ። ስዊድን ፡ የምንገኘው ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አገልጋዮች ፡ ሌሎችም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሠራተኞች ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ለንጉሣዊ፡ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ታላቅ ፡ ኀዘናችንን ፡ በትሕትና ፡ እንገልጻለን ።

* * *

በሜክሲኮ ካሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጉዳይ ፡ ፈጻሚ ፡ ከአቶ ፡ ዮሐንስ ፡ ረዳእግዚእ ፡ የተላከ ።

በደረሰው ፡ ከባድና ፡ መራር ፡ ኀዘን ፡ ተካፋይነታችንን ፡ በታላቅ ፡ ትሕትና ፡ እንገልጻለን ።

* * *

በዋሽንግቶን ፡ ከተማ ፡ ከሚገኙት ከክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ዘውዴ ፡ ገብረሥላሴ ፡ የተላከ ።

በተወዳጁ ፡ ልዑል ፡ ጌታዬ ፡ ዕረፍት ፡ ምክንያት ፡ በግርማዊነትዎና፡ በሀገራችን ፡ ላይ ፡ በደረሰው ፡ ድንገተኛ ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ የተሰማንን ፡ መራራ ፡ ኀዘን ፡ በታላቅ ፡ ትህትና ፡ እገልጻለሁ ።



* * *

ከአሥመራ ፡ የፌደራል ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ መማክርት ፡ የተላከ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ፡ በተወደዱ ፡ ልጅዎና ፡ ጌታችን ፡ ልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍን ፡ ሐረር ፡ ድንገተኛ ፡ ዕረፍት ፡ ምክንያት ፡ በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ በደረሰው ፡ ከባድ ፡ ኀዘን ፡ እንባችንን ፡ እያፈሰስን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ጤንነት ፡ ይስጥልን ፡ እንላለን ።

* * *

በዋሽንግቶን ፡ ከሚገኙ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተማሪዎች ፡ የተላከ ።

በተወደዱት ፡ ልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍን ፡ ሐረር ፡ ድንገተኛ ፡ ሞት፡ በዋሽንግተን ፡ ከተማ ፡ የምንገኝ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ተማሪዎች ፡ ከባድ ፡ ኀዘናችንን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ እንገልጻለን ። እግዚአብሔር ፡ ግርማዊነትዎንና ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብን ፡ ያጽናልን ።

* * *

ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ከሚገኙ ፡ ተማሪዎች ፡ የተላከ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ፡ የልዑል ፡ መኰንን ፡ ዕረፍት ፡ በታላቋ ፡ ብሪታንያ ፡ በምንማር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተማሪዎች ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ኀዘን ፡ ጥሎብናል ። የግርማዊና ፡ የንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብዎ ፡ መሪር ፡ ኀዘን ፡ ተካፋይ ፡ ነን ።

* * *

በስዊድን ፡ አገር ፡ ከሚገኙ ፡ ተማሪዎች ፡ የተላከ ።

በልዑል ፡ መኰንን ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ አሳዛኝ ፡ ዕረፍት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድንጋጤ ፡ ሰምተነዋል ። ልዑል ፡ መኰንን ፡ ታላቅ ፡ መሪያችን ፡ ነበሩ ። ስለዚህ ፡ የኀዘን ፡ ተካፋይ ፡ መሆናችንን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ እንገልጻለን ።